እግዚአብሔር

ለምን ዝም ይላል?

ከመለሰ ወጉ

June 1990

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?

ETHIOPIAN OUTREACH MINISTRY
P.O. BOX 3413
YORK, PA 17402
U.S.A

printed in the United States of America



ጌታን ላስተዋወቁኝና በመንፈሳዊ ሕይወቴ ላሰደጉኝ፣ መንፈሳዊ እናቴ፣ ለሚስ አልሜ ሃልቪ የምስጋናዩ መግለጫ እንዲሆን፣ ይህን መጽሐፍ በማስታወሻ መልክ አቀርበለሁ።

ማውጫ

እግዚአብሔር ለምን ርቆ ቆመ? 9

ያለ አግባብ ስንኑቀፍ፤

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? 18

በብቸኝነት ስንሰቃይ፣

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? 27

በሕመም ስንሰቃይ፣

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል 38

በእጦት ምክንያት ስንሰቃይ፣

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይለል? 49

የምንወደው በሞት ሲለየን፣

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? 64

ያልጠበቅነው ከፋ ነገር ሲደርስብን፣

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? 72

ትዳራችን ሲናጋ፣

እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? 80

ምን እናድርግ፣

እግዚአብሔር ዝም ያለ ሲመስለን? 92

መግቢያ

ኢየሱስ የመጪ ረሽውን የሞት ጽዋ ሰመጠጣት ከመቅረቡ በፊት፤ ብዙ የመከራ ድልድዮችን አልፎአል። ከመጪ ረሽው ሰይ ሲደርስ ግን እግዚአብሔር የረሰው በሰ መበሰው «እምሳኬ፤ እምሳኬ ሰምን ተውከኝ» ሲል ጮኸ። ኢየሱስ በመከራው ወቅት እግዚአብሔር ፍጹም የረከው ከመሰሰው፤ እኛም በልዩ ልዩ ፈተና ውስጥ በናልፍ እግዚአብሔር የረሳንና ዝም ያለን ቢመሰለን፤ ይህን ያህል እይፈረድብንም።

ኢየሱስ ሁሱም ያሰው ባለጸጋ ጌታ ቢሆንም፤ በማጣትና በኑሮ ጥበት ምንክያት የሚደርስብንን በቃይ ለመቅመስ ቀደም ሲል ፈቅደ በሰ እኛ ድህ ሆኗል። ሌሳው ቀርቶ እራሱን የሚያስጠልልበት የራሱ የሆነ ቤት እንኳን አልነበረውም። በሰዚህ ጌታን «በእጦት ምክንያት ያሰውን በቃይ እንተ በሳሰሰፍክበት እታውቀውም» ልንሰው እንችልም።

ኢየሱስ በነበረው እጭር የአገልግሎት ዘመን፤ ሰሰዎች ከሰጠው አገልግሎት መካከል እንደኛው፤ በሽተኞችን መፈወስ ነበር። ሁልጊዜ መንፈሳዊ ችግር ሳሰባቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን፤ በሰጋቸው ሰሚሰቃዩትም እውነተኛ ርህራሄና ፍቅር ነበረው። ዛሬም ቢሆን በሕመም ምክንያት የሚሰቃዩትን ህመምተኞች እያየ ችሳ የማለት ልብና ባህሪ የለውም።

አልአዘር በሞት ሲለይ፤ እህቶቹና እንዲሁም የሚወዱት የአካባቢው ሕዝብ በአልአዘር ሞት ምክንያት የተሰማቸውን ውስጣዊ ህዘን ተመልከቱ ዕንባውን እንደፈሰበ እናውቃለን። ኢየሱስ የሚወዱትን በሞት ማጣት፤ ህዘኑ ምን ያህል ወደ ሰው ልብ ውስጥ ሰርጉዶ እንደሚገባ በሰሚያውቅ፤ በዚህ ሕይወት ውስጥ ሰሚያልፉትና እርዳታውን ለሚፈልጉ ሁሉ ሰማያዊ መጽናናትን ይሰጣቸዋል።

ኢየሱስ የቀመሰውን በመቅመሰችን፤ በለፈባቸው መንገደች በማለፋችን ደስ ቢለንም፤ ሥጋ ለባሽና ደካማዎች በመሆናችን፤ በልዩ ልዩ ፈተና ስንታሽ <u>እግዚአብሔር የሸሸን</u>፤ <u>እግዚአብሔር ዝም ያለን</u> ይመስለናል። ይህን ዓይነት ስሜት የሚሰማን እኛን ብቻ ባይሆን፤ ኢየሱስ እራሱም ተሰምቶታል። «እምሳኬ፤ እምሳኬ ሰምን ተውከኝ?» ብሎ የጮኸው፤ በዚያ መከራ ውስጥ የእግዚአብሔር እብን ርህራሄና

ፍቅር ማየት በሰተሰነው ነበር።

አልፎ አልፎ አንግዳ ትምህርቶችና ሃሳቦች በአከበሪያችን ብቅ ብቅ ማሰታቸው አይቀርም። እነዚህ እንግዳ ትምህርቶች፣ ከርበቶበ የሌሰውን በህሪ አንደሰው፣ ያልተናገረውን እንደተናገረ አድርገው ያውጃሉ። በዚህ ምክንያት በመከራ ውስጥ በሚያልፈው ሰይ በመፍረድ፣ እግዚአብሔርን ርህራሄ የሌሰው ጨካኝ አምሳክ ብቻ እንደ ሆነ አድርገው በማቅረብ፣ ብዙዎች ከክርስትና ሕይወት እንዲሸሹ ያደርጋሉ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጠቀስናቸው አንዳንድ ሃሳቦች፣ በአእምሮአችን ሰሚመሳሰሱት ጥያቄዎቻችንን ሁሉ መልበ ይሆናሉ በንልም፣ ከሞሰ ጎደል፣ አንዳንድ ሃሳቦች ይሰጣሉ ብለን በመገመት ያሰፈርናቸውን ነጥቦች በጥሞና እንድትመሰክቷቸው አንጋብዘችኋለን።

1

እግዚአብሔር ለምን ርቆ ቆመ?

እግዚአብሔር «ዓሰምን ከወደደ» ሰምን ዓሰም በመከራ ውስጥ በትጪነቅ እያየ ዝም ይሰል? «ፍቅር» ከሆነ፣ የሚያፈቅራቸው የሰው ልጆች ሊቋቋሙት በማይችሉት ኃይል ሲገፉ፣ በጎ ያልሆነ ነገር በሕይወታቸው ሲደርስባቸው በወቅቱ ደርሰ የማያስወግድሳቸው ለምን ይሆን? በልጁ ደም የገዛቸው ክርስትያን ልጆቹ ደግሞ መከራ እንደ ዝናብ ሲወርድባቸው የማያስጥሳቸው ለምንድነው?

በዓለም ሰይ ብዙ በጎ ያልሆኑ ነገሮች ተፈጽመዋል፤ አሁንም እየተፈጸሙ ናቸው፤ ወደፊትም ይፈጸማሉ። በየጊዜው በጦርነት፣ በረሃብ በጎርፍ፣ በመሬት መንቀጥቀጥ፣ በእሰት እደጋና በመሰሰሉት ምክንያቶች ሕይወታቸውን የሚያጡ ሰዎች ቁጥር ጥቂት አይደለም። በየሆስፒታሉ በማይድን በሽታ ተይዘው የሚሰቃዩና ተስፋ ቆርጠው የሞትን ጽዋ ለመ ቅመስ የሚጠባበቁ ሕፃናት፣ ወጣት ልጆች፣ በመከከለኛ ዕድሜ ያሉና

እንዲሁም በዕድሜያቸው ጠና ያሉ ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። የብዙዎች ጥያቄ «ለምን ይሄ እንዲህ ይሆናል?» የሚል ነው።

በእግዚአብሔር ላይ ምሬት ያደረባቸው እንደንድ ለዎች፣ «እግዚአብሔር መከራና ስቃይ በሰው ላይ እንዲበረታ ለምን ፈቀደ? እምለክ ከሆነ፣ ኃይል ሰላለው ክፉን ማስወገድ በቻለ ነበር! እንዲሁም «ደግ እምለክ» ከሆነ ደግሞ ክፉ ነገር በሰዎች ላይ እንዲደርስ ባልፈቀደም ነበር። ሰለዚህ እግዚአብሔር «ኃይል ያለው እምለክ» ባይሆን ይሆናል፤ ወይም «ኃይል ያለው እምለክ» ከሆነ ደግሞ «ደግ እምለክ ሳይሆን ይሆናል» ሲሉ አሰተያየታቸውን ይሰጣሉ።

አንድ ጊዜ አንድ የሚያሳዝንና የሚሰደነግጥ ዜና የደረሰባቸው የእናትና የአበት ታሪክ አሰታውሰለሁ። ዕድሜዋ ወደ 30 ዓመት የተጠጋ፣ በጠባይና አንዲሁም በመልኪ ውብ የሆነች ሴት ልጅ የነበረቻቸው ወላጆች ነበሩ። ይህቺ አንዷ ልጃቸው በታታሪነቱና በመንፈሰ ዊ ሕይወቱ የሚደነቅ አንድ ወጣት አግብታ አራት ልጆች ወልደ ትኖር ነበር። ለመንፈሰ ዊ አገልግሎት በሙሉ ጊዜ ሰመውጣት ከእግዚአብሔር ጥሪ እንደደረሰባቸው ከረጋገጡ በኋላ፣ ለአገልግሎት የበለጠ ለመዘጋጀት መጽሐፍ ቅዱሰ ትምህርት ቤት ገቡ። ትምህርታቸውንም እንደጨረሱ ጌታ ወደ ጠራቸው ሥፍራ ወንጌል ባልደረሰባቸው ሕዝቦች ለመሰበክ አገልግሎታቸውን ጀመሩ።

ለጥቂት ወራት ያህል በአገልግሎት ላይ እንደቆዩ፣ አንድ ቀን በአገዲት ትንሽ አይሮፕላን ከአንድ ከተማ ወደ ሌላው ከተማ ሲበሩ ድንገት አደጋ ተፈጥሮ አይሮፕላኗ ተቃጥሳ ከመራት ሰትወድቅ ከአንዲት ከአሥር ዓመት ልጃቸው በቀር ሁሉም ወዲያው ተቃጥለው ሞቱ።

የልጅቷ ወላጆች እንባቸው መፍሰሱ፣ ልባቸው መበበሩ ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ጥያቄ በአዕምሮአቸው መፈጠሩ አይቀርም። «ስህተቱ የማን ነው? ለምን ይህ እልቂት ሆነ? ከዚህ ውስጥ ምን በጎ ነገር ይወጣል? በጎ ነገርስ ቢወጣ ሰው ሳይሞት ሊሆን አይችልም ነበር ወይ? መልካም ነገር ለማድረግ ሕይወታቸውን በሰጡ ለዎች ላይ ክፉ ነገር ለምን ይደርስባቸዋል? ለመሆኑ እግዚአብሔር ትክክለኛ ፈራጅ ነው? ሰዎች በመከራ እንዲያልፉ አድርጎ በማሰጨነቅ የሚያገኘው አምነትና ክብር ምን ያደርግለታል?» የሚል ጥያቄ በዓዕምሮአቸው ሳይመላለስ አይቀርም።

ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች እንኳን በመከራ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ቀርቶ ሌሎች ሰዎችም ቢጠይቁ ከአግባብ ውጪ የሆነ ጥያቄ ጠይቀዋል አያሰኛቸውም። ከሁሉም የተሻለው ጥያቄ ግን፣ በጎ ነገር ሰናይ፣ በሀዘንና በሞንቀት በተከበብንበት ጊዜ በእግዚአብሔር መታመን እንችሰለን? ከመከራና ከሀዘን ውስጥ በጎ ነገር ይወጣል ብለን ተማምነን መጠበቅ እንችለለን? የሚለው ጥያቄ ነው።

በሰው ላይ የሚደርሱት እንዳንድ ክፉ ነገሮች እንደ ድቅድቅ ጨለማ አሰፈሪዎች ናቸው። እንደንድ ችግሮች በጣም ጥልቅ ያሏቸውና ፍጹም ተስፋ የሚያስቆርጡ ከመሆናቸው የተነሳ «እግዚአብሔር ሆይ ለምን ፈጠርከኝ?» የሚያሰኙ ናቸው።

አልፎ አልፎ መሰመር የለቀቀ ትምህርት በተባራሪ ያገኙ እንደንድ ሰዎች፣ እምነታቸውን በተሰሰተ ነገር ላይ ያሰርፋሉ። ከነዚህም መካከል እንደንዶችን ለመጥቀስ እንሞክራለን።

1) «ክርስትያን ስትሆን ችግርህ ሁሉ ይጠፋል»

«ወደ ጌታ ብትመጣ ምንም ዓይነት መከራና ችግር አይደርስብህም» በማለት የማያምነውን ሰው ለመለወጥ ሙከራ ከደረግን ትልቅ ሰህተት እየሠራን ነው። «አዲሰ ፍጥረት እንደምንሆን» እንጂ ከፈተና ነፃ ሆነን እንደምንኖር መጽሐፍ ቅዱሰ ተስፋ አልገባልንም። በመጪ ረሸው የዘለሰምን ሕይወት እንደሚሰጠን እንጂ፣ በምድር ላይ የአበባ ምንጣፍ እንደሚዘረጋልን ቃል አልገባልንም። እንዲያውም ለእማኝ የመረጠው መንገድ በጣም ጠበብ ከመሆኑ የተነሳ ጉዘው አሰቸጋሪ ነው።

እንድ ሰው ከርስትያን ሲሆን ስጋዊና መንፈሰ ዊ ችግሩ ተወግደ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራል በማለት የተሳሳት ትምህርት የሚያሰተምሩ አሉ። በተቃራኒ ግን እማኝ «መከራ እንደሰበት» መጽሐፍ ቅዱሰ (ዩሐ 16፣33) ይናገራል። ከመከራና ከችግር እንዲሁም ከሀዘን ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆን የምንችለው ወደ ሰማያ ዊ ቤታችን ስንሄድ ብቻ ነው (ራዕይ 21፣4) እንጂ በዚህ ምድር አይደለም።

ታዲያ ከርስትያን ከማያምን ሰው ምን የተለየ በጎ ነገር በምድር ላይ ይኖረዋል? አዎን ብዙ ነገር አለው። ከርስትያን የሚወደውና ችግሩን የሚያደምጥለት እንደሁም በአሰፈላጊው ጊዜ አሰፈላጊውን እርዳታ

የሚያደርግለት ስማያዊ አበት አለው (ዕብ 4፤16)። እንዲሁም በአብ ቀኝ ቆሞ «ስለ እርሱ የሚማልድለት» (ዕብ 7፤፤5) ሊቀ ከህን አለው። ከርስትያን ልክ እንደማያምኑት በመከራና በችግር ሕይወት ውስጥ ያልፋል። ይሁን እንጂ ከሌሎቹ የሚለይበት ነገር ቢኖር እርሱ እርዳታ ቢጠይቅ እርዳታ የሚሰጠው አምላክ ያለው በመሆኑ ብቻ ነው።

ሃዋርያው ጳውሎስ አልፎ አልፎ «የሚያሰዝን ነገር» ያጋጥመው ነበር። ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ደስተኛ ነበር (2ኛ ቆሮ 6፤10)። ብዙ የሚያስፈልገውን ነገር በሕይወቱ ባያገኝም፤ በሁሉም ነገር መርከትና መጥገብን በሕይወቱ የተሰማመደ በው ነበር (ፊሊጵ 4፤11–12)። ጳውሎስ በችግር ውስጥ እንኳን እያለፈ በሕይወቱ መርከትን ማግኘት የቻለው እግዚአብሔር ረዳቱ ስለሆነ ብቻ ነው (ፊሊጵ 4፤13)።

ከመከራ ማንም ነጻ መሆን አይችልም። በተለያየ ጊዜና በተለያየ ሁኔታ ሁሉም መከራን ይቀምሳል። የምንወደው በው እስከ እለን ድረስ የመከራን ጽዋ መቅመሳችን አይቀርም። ይሽውም፤ ከመከራ ጽዋችን መከከል እንደኛው የምንወደውን ሰው በሞት ወይንም በሌሳ ምከንያት ያጣን እንደሆነ ግልጽ ነው።

ደስታን ስማወቅ በቅድሚያ ሀዘንን መቅመስ ያስፈልጋል። ሀዘን ሠርጉደ ወደ ውስጣችን ስገባ መጠን፤ በዚያው ልክ ደስታን መሸከም እንችሰለን። ወደድንም ጠሳንም፤ በተለያየ መልከና ጊዜ ደስ የማይለን ነገር በሕይወታችን ይደርሰል። ይህን የምንስው ነገርን አጪልሞ ስማየተና ደስታን ከውስጣችን ለማጥፋት አይደለም።

ጌታን በቅጡ በሕይወቷ ያወቀች እንዲት የ15 ዓመት ወጣት በመከራ ውስጥ ስታልፍ ስጀደኛዋ የፃፈችውን ደብዳቤ ከዚህ ስታች እንመልከት።

«----ይህን ደብዳቤ የምጽፍልሽ በጋይል ታምሚ ከሆስፒታል ውስጥ ሆኜ ነው። ሕመሜ በጣም ስለ ሚያስጨንቀኝ እንቅልፍ ከተኛሁ አንድ ሰምንት አልፎኛል። አሁን እንደማየው ከሆነ፤ ሆስፒታል ብዙ ጊዜ የምቆይ ይመስለኛል። ጌታ ድንቅ አይደለም ይህን ዓይነት ሆስፒታል ለእኔ ሊያዘጋጅልኝ? ህኪሞች የሚያደርጉልኝ ሕከምና በጣም ቢያሰምመኝም፤ ስለ ሚያደርጉልኝ ዕርዳታ ሁሉ አመስግናቸዋለሁ። ጌታ ኢየሱስ ለእኔ ብዙ ስለ አደረገልኝ፤ የማመሰግንበት ቃሳት ያጥረኛል።»

«የእናቴም ሕመም በጣም እየከፋ ነው። ሕይወቷ የቆመው በአሁኑ ወቅት በመሳሪያ ጋይል ብቻ ነው። የተኛችው እዚሁ እኔው ከለሁበት ሆስፒታል ቀጥሎ ከሰው ፎቅ ሳይ ነው። ሕይወቷን ስማትረፍ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ ህኪሞች ያስቡት የልብ ቀደ ጥገና ለማድረግ ነው።

የአባቴም የመጠጥ ሱስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበሰ ነው። እኛን ስድስት ልጆቹን ማሰደግ አይፈልግም። እናቴ እንድ ነገር ብትሆን፤ በቤተሰባችን ውስጥ ትልቋ ልጅ እኔ በመሆኔ፤ ጠቅሳሳ የቤተሰቡ ጋሳፊነት ከእኔ እራስ አያልፍም። ከርስትያን በመሆኔ በጣም ደስ ይለኛል። ምክንያቱም ያለ ከርስቶስ ድጋፍና እርዳታ ይህን ሁሉ መታገስና መሸከም ሰልቻልኩም ነበር።

የቤታችንም ጣራ እንደምታውቂው መፈራረሱ ነው። የማልፍበትን ችግርና መከራ ሁሉ ጌታ እየሱስ ስለሚያውቅ ምን ማድረግ እንደሚገባኝ እርሱ ይመራኛል። ስእርግጥ ስጣም እወደዋለሁ፤ ከርስትያን በመሆኔም እደስታለሁ» አለች።

ይህች ወጣት ልጅ በሕይወቷ ምንም በጎ ነገር አታይም። ሁሉ ነገር የከፋና ጨለማ ነው። ይሁን እንጂ በመከራዋ ውስጥ እንኳን ሕይወቷ በምስጋና የተሞሳ በመሆኑ እንደ ጸሀይ የሚያበራ መንፈሳዊ ሕይወት ይታይበታል። ይህቺ ወጣት ይህን ደብዳቤ ስትጽፍ፤ ደብዳቤዋ በመጽሐፍ ተጽፎ የብዙዎችን ሕይወት እንደሚበርክ ያኔ አልተረዳችም ነበር። ደብዳቤዋን የሚያነቡ ሁሉ ከሀዘናቸው እንደሚጽናኑና ከፍተኛ ትምህርትም እንደሚያገኙበት በጣም ግልጽ ነው።

ይህች ወጣት «ስምን ስእኔ ይሄ ሁሉ ደረሰ» በማለት ልትሰለቹ፤ እግዚአብሔርንም ስማማረር ልትጠይቅ፤ እንዲሁም ስለ እራሷ ልታዝን ሊገባት፤ ያ ሁሉ ቀርቶ ስሀዘኗ መከከል እግዚአብሔርን ታከብር ነበር።

ስለ ደረሰብን ነገር ከማዘንና ከማልቀስ ይልቅ፤ ነገር ሁሉ በጪለመብንና በከስደብን ጊዜ ለሕይወወታችን ፈውስ ይዘልን እንደሚመጣ ስመተማመን እምሳከችንን ለመከተል ፈቃደኞች ነን? እግዚአብሔር እንዴት ሊያጽናናን ይችሳል? እውን ሁኔታዎች እንኳን ባይለወጡም የእርሱ መገኘት ብቻ ያጽናናል።

ክርስትያን ስለሆንን ብቻ መከራችን አይጠፋም። ችግርና ፈተና ይደርስብናል። ይሁን እንጂ ችግራችንን የምንረደበት ጥበብና ኃይል እግዚአብሔር ይሰጠናል። ስለማችንና እምነታችን፣ በተሰይ በመከራ አብዝተን በምንፈተንበት ጊዜ ይጠፋብን ይሆናል። ሆኖም እንደ ተሰፈው መጠን ጌታ ጨርሶ አይጥለንም።

2) «ችግር የበዛብህ ኃጢአት ሠርተህ ይሆናል!»

ችግር የደረሰበትን ሰው በማጽናናትና በመደገፍ ፈንታ፣ የፍርድ ቃል የሚሰነዝሩ ክርስትያኖች ብዙዎች ናቸው። ክርስትያን በመከራና በችግር ውስጥ ሲያልፍ፣ ችግሩን ገለልሞ ለወንድሞቹና ለእህቶቹ እንዳይናገር የሚደብቀው፣ «ይህ ሁሉ የደረሰበት የተደበቀ ኃጢአት ቢኖርበት ነው» በማለት እከሰሰለሁ እያለ ነው። በዚህ ምክንያት ከደረሰበት መከራ ይልቅ የብቸኝነት ሕይወቱ የከፋ ይሆንበታል።

መልከምና ፍጹም ጤናማ መንፈሳዊ ሕይወት እየኖርንም ቢሆን፣ ከፈተናና ከችግር ነፃ አንሆንም። ጴጥሮስ ጽድቅ እንኳን እየሠራን መከራ እንደምንቀበል ይናገራል (1ኛ ጴጥ 3፣14)። አንዳንድ ጊዜ መከራ የምንቀበለው ሰቅጣት ሰይሆን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ በለሆነና የእምነታችን መፈተኛ በመሆኑ እንደሆነ ሃዋርያው ጴጥሮስ ይገልፃል (1ኛ ጴጥ 3፣17)።

እርግጥ ነው «ከፉን በሚያደርግ ሰው ነፍሱ ሁከት፣ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል» ይላል (ሮሜ 2፣9)። ይሁን እንጂ መከራና ጭንቀት ደግን በሚያደርጉትም ሰዎች ላይ ሊደርስ ይችላል። «በእውነትም በክርስቶስ ሊየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ» (2ኛ ጢሞ 3፣12) ይላል።

ለመሆኑ ቦጥንቃቄ ሕይወታቸውን በሚመሩ ክርስትያኖች ላይ መከራና ጭንቀት እንዲደርስባቸው የሚፈቅደው ለምን ይሆን? ከብዙ ምክንያቶች መካከል ከዚህ በታች ጥቂቶችን እንገልፃለን፣

(ሀ) ንጹህን ሊያደርገን (2ኛ ቆሮ 7፣9–11)
(ለ) ትዕግሥትን ሊያስተምረን (ሮሜ 5፣3፤ ያዕ 1፣3)
(ሐ) ትህትናን ሊያስተምረን (2ኛ ቆሮ 12፣ 7–10)
(መ) በእግዚአብሔር እንድንታመን (2ኛ ሮሜ 1፣8–9)

ስለሆነም በችግር ውስጥ የሚያልፈውን ሁሉ «በኃጢአቱ ምክንያት ይሄ ደረሰበት» ስማለት መፍረድ ትክክል አይደለም። በቅርቡ አንድ ልቡ በጣም ያዘነበት ሰው፣ ክርስትያኖች ምን ያህል እንደ ፈረዱበትና እንዳሰዘኑት ደብዳቤ ጻፈልኝ። ደብዳቤውን በአጭሩ ከዚህ በታች አንበቢዎች እንዲያዩት አበፍራዋለሁ።

«–– ብዙ ጊዜ የፍቅርና የናፍቶት ሰላምታዩን ገልጬ ለመጻፍ ፈልጌ አድራሻህን ሰሰገኝ ቀረሁ። ከሁሉም በላይ ልጽፍልህ የፈለግሁበት ምክንያት በሕይወቴ ብዙ ፈተናዎች ተፈራርቀብኝ፣ ለሰበት ዓመት ያህል ብዙ ስቃይ ደርሰብኝ ሰችግር ላይ በለነበረኩ፣ ይህን ኑ ሰጫውትህ ፈልጌ ነበር።»

«ጋሽዬ! ጌታ ልጆች ሰጠኝ፣ እግዚአብሔር ይመስገን። የመጀመሪያዋ ልጄ ቤት ነች። እርሷም ስትወለድ ዘመጠን በላይ ደስ አለኝ። ግን ብዙም ሳይቆይ ደስታዬ ወዲያው ወደ ሀዘን ተለወጠ። በጣም ቆዘምኩኝ።»

«ህኪሞች ያለምንም ምክንያት አንጎሏን አፐራሲዮን አደረጊት። አፐራስዮን ከሆነች በኋላ አትናገር፣ አትሂድ፣ አትቆም። ለአሥር አመት በኢኮኖሚም በአዕምሮም በቆዝም ቆየሁ። ከሰው ዘንድ ተሰፋ አጥቼ፣ እግዚአብሔርን እሰከ እሁን እየጠበቅሁ ነው»

«ያለሁበት ቤተ ክርስትያን ልጆቹን በቤተ ክርስትያን ሥርዓት መሠረት በሰ አለስጠመቀ፣ ሁለተኛም «የመጀመሪያ ልጁ ለምን እንዲህ ሆነች? የተደበቀ ኃጢአት ቢኖረው ይሆልና ቤተ ክርስትያን ማወቅ ያስፈልጋታልና ንስሀ ይግባ» በማለት እኔንና ባለቤቴን ከመዘምራንነትና ከአባልነት ሰረዙን። እኛም ሥጋዎች በመሆናችን ተበሳጭተን በቤታችን አገልግሎት ጀመርን። ይኸውልህ ያለ ቤተ ክርስትያን እግዚአብሔር በለጠነ ጸጋ በትንሽ ጎጆአችን ውስጥ በመጽናናት እንገኛለን። አንተም ለሰ ልጄ ጸልይልኝ።»

«––– ከአሥራ ሦስት ዓመት በፊት የእግዚአብሔርን ቃል በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተህ በሕይወትህ ያሰፍከባቸውን ፈተናዎችንና ሕይወቶችን በታስተምረኝ ኖሮ ዘራ የተፈራረቀብኝን ፈተናዎች ለመቋቋም ባልቻልኩም ነበር። ጌታዬ አቁሞኛል፤ ጌታ ገና ሲመርጠኝ ለነፍሴ የሚሆን መሠረት ያሰው ትምህርት ሰጥቶኛልና «ሰይጣን

ልትቢጭረኝ አትችልም» በማለት አስከዛሬ ቆሜአለሁ።

«--- ምንም እንኪን ዘራ ወደ ቅዱስ ቅዱሰን መግባት የተለጠው ለእኛ ለቅዱሶች ነው፤ አናንተ ግን ኃጢአተኞች ናችሁና ንስሀ ስለ አልገባችሁ ከአጥር ውጪ ቆማችሁ ጸልዩ ቢሉንም፣ ጌታ መጥቶ ወደ ቅዱስ ቅዱሰን በልጁ ደም አሰገብቶናል። በውስጤ የሚያብለለለኝ የአገልግሎት ጥማትና ናፈቆት አንድ ቀን አርሱን የማገለግልበት መቅደሰ አገኛለሁ ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ»

በጌታ ወንድምህ።

የእግዚአብሔርን ቃል በደንብ በለመማርና በለማወቅ «በሕይወቱ ችግርና ፈተና የሚያጋጥመው ኃጢአተኛ ስለሆነ ነው» በማለት መጽናናት የሚገባቸውን በማጽናናት ፈንታ መከራቸውን የሚያበዙ ክርስትያኖች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም። በመታቀፍ ፈንታ ተገፍተው፣ ልባቸው ተሰብሮ ከክርስትያን እንድነት የወጡትን ቤታቸው ይቁጠራቸው።

ችግርና ጭንቀት ሲደርሰብን የሚያሰየው ኃጢአተኞች መሆናችንን ሳይሆን፣ ሰዎች መሆናችንን ብቻ ነው። እንዲያውም መከራና ሰቃይ የሚበዘባቸው ኃጢአተኞች ሰይ ሰይሆን፣ በቅድሰና ሕይወታቸውን ለመምራት በሚሞክሩት ለዎች ሰይ ነው።

መከራና ጭንቀትን እንደ ኢዩብ የቀመለ ሰው በዚህ ምድር የለም። ለዋያቄው ሁሉ መልሰ አልነበረውም። ለምን እንደሚሰቃይና በመከራ ውሰጥ እንደሚያልፍ አልገበውም። ጊደኞቹም በተሰሰተ አሰተሰሰባቸው ይፍረዱበት እንጂ ትክክለኛ መልሰ አልነበራቸውም። ኢዮብ በመከራ ውስጥ ያስፈው ሰለ ኃጢአቱ ነው እንደንል፣ የእርሱን ዓይነት የተቀደሰ ሕይወት ያለው ሰው አልነበረም።

በክርስትያኖች ሕይወት መከራና ጭንቀት እንዲደርስ እግዚአብሔር የሚአቅድበት በዙ ጥሩ ምክንያቶች አሉት። እጅግ ያማረ ሕይወት ያላቸው ክርሰትያኖች በፈተና ውሰጥ ያልፋሉ፤ ይሁን እንጂ ያ ችግራቸው የበለጠ ወደ ክርሰቶስ ሲያቀርባቸውና ሲያሰጠጋቸው አይተናል። «የክርስቶስ በመሆናችሁ ወደ ዘለለማዊ ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ራሱ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበሰችሁ በኋሰ ፍጹሞች ያደርጋችኋል፤ ያጸናችሂል፤ ያበረታችኋልም» (1ኛ ጴጥ 5፣10)።

በመከራ ሰንጪነቅ «የት ነው እግዚአብሔር? አንድ ነገር ለምን

አያደረገም?» የከፋ ሁሉ ነገር ምንጭ የሆነ ይመስል፣ «ጌታ ሆይ ይህ ለምን በእኔ እንዲደርሰ ታደርጋለህ? ጌታ ሆይ ለምን አትረዳኝም?» በማለት የጭንቀት ጩኸት የምናሰማ ጥቂቶች አይደለንም።

ኢሰያሰ «የእሥራኤል አምላክ መድኃኒት ሆይ፣ በእውነት እንተ ራስህን የምትሰውር አምለክ ነህ» (ኢሰ 45፣15) ሲለው ዳዊት ደግሞ «አቤቱ ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራም ጊዜ ለምን ትሰወራለህ» (መዝ 10፣1) ሲል ይጠይቀዋል። የእኛም ጥያቄ ከዚህ የተለየ አይደለም።

በመከራና በጭንቀት ውሰጥ ስናልፍ ልንረደቸውና ልናውቃቸው የሚገቡ እውነቶች አሉ፤

--በሰው ሰይ የሚደርሰው ከፋ ነገር ሁሉ አመንጪው እግዚአብሔር አይደለም። እግዚአብሔር በሰው መከራና ጭንቀት ደሰ የሚሰው አምለክ አይደለም።

---በጭንቀታችንና በመከራችን ጊዜ አጠገበችን መኖሩ በማይሰማን ጊዜ ሁሉ እንኪን ከእኛ ጋር ነው። ችሰ እንደማይለንና እንደ ማይተወን ቃል የገባልን ሰለሆነ ሁልጊዜ አጠገበችን ነው።

-- እግዚአብሔር እርምጃችንን ሁሉ እንቅፋት የሌለበት፤ ከመከራና ከጭንቀት ሁሉ ነፃ እንደሚሆን ተሰፋ አልገበልንም። ይሁን እንጂ ከፋ አንኪን ቢገጥመን ለበጎ እንደሚያደርግልን ተሰፋ ለጥቶናል (ሮሜ 8፣28)።

--እግዚአብሔር ፍጹም ፍቅር፣ ፍጹም አምሰክ፣ ከኃይል ሁሉ በሰይ ኃይል ያለው፣ እንዲሁም በአንድ ጊዜ ሁሉም ቦታ መገኘት እንደሚችል እንመን። ያንንም አምነት አጥብቀን እንያዝ።

--እርሱን ብቻ እንታመን። «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፣ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፤ እርሱም ጎደናህን ያቃናልሃል» (ምሳ 3፣5-6)።

2

ያለ አግበብ ስንነቀፍ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?

የእሥር ዓመቱ ልጁ ዮሴፍ፣ ገና ህጻን ልጅ ሆኖ ጥፋት አጥፍቶ ከበድ ቅጣት እንኳን ሲሰጠው ያለእንደኾ ማጉረምረም ቅጣቱን ይቀበላል። ሰያጠፋ ያሰ አግበብ ከተቀጣ ግን ቅጣቱ ምንም ያህል ትንሽም ቢሆን፣ ይጎዳዋል፤ ይቆረቁረዋል፤ በኃይልም ያስከቅዋል።

ይህን ዓይነት ስሜት ያለው ዮሴፍ ብቻ አይደለም። ሁሳችንም ያለ አግበብ ስንወቀስ፣ ስንነቀፍ፣ ጠሳቶች ሲነሱብን ቅር ይለናል፤ ይጎዳናል። ብዙ ጊዜ እራሳችንን ከምንከሳከል ይልቅ «ፈራጁ እግዚአብሔር የት ነው ያለኸው? ያለ አግበብ ስንወቀስ፣ ያለ አግበብ ስማችንን በክፉ ሲያነሱት አታይም? ፈጥነህስ አትፈርድም?» በማለት ወደ እግዚአብሔር እሮሮአችንን እናሰማለን።

ስንታየሁ ሰብዙ ዓመት ከጌታ ጋር የተራመደ ወንድም ነው። በአገልግሎቱ ጌታ ሲባርከው ያዩና የተመለከቱ ብዙ ክርስትያኖች ደስ ይሰኙበታል። ከስንታየሁ ጋር በቅርብ አብረውት የሚያገለግሉት እንዳንድ ወንድሞች ከየአቅጣጫው ስለ እርሱ የሚሰሙት የምስጋናና የሙገሳ ቃል ደስ ከሚያሰኛቸው ይልቅ እያስቆጣቸው ሄደ። በሙቤ ሰይ እንደ አጉረመረሙት እንደ አሮንና እንደ ማርያም «እግዚአብሔር በስንታየሁ ብቻ ነው እንዲ የሚሠራው? በእኛስ አይሠራም እንዲ? እኛስ? ስንታየሁ፣ ስንታየሁ ብቻ የሚሰሰው» በማስት ውስጥ ውስጡን ማጉረምረም ጀመሩ።

ስተንከል መንገድ የስንታየሁን ስም ጭቃ የሚቀቡበትን ዘዴ መፈለግ ጀመሩ። ከርስትያኖች፣ እንድያውም አገልጋዮች በመሆናቸው፣ ፊት ሰፊት «ስሙን እናጉድፈው» ብለው አይነሱም። መንፈሳዊ ምክንያት መፈለግ አለባቸው። ከመከከሳቸው ጀማሪው እንዲ ይሆናል። ቆረቀቀ መንገድ ስለ ስንታየሁ መጥፎ አስተያየት መወርወር ይጀምራል። ሌሳውም ይቀጥልና «እሪ እኔም እንዲህ ተሰምቶኛል» ይላል። በዚህ ሁኔታ የጌታ ቤት ተቆርቋሪዎች ስመምስል በቅናትና በጥላቻ ተንከሳቸውን መሸረብ ይጀምራሉ።

ስንታየሁ ከርስትያን እጮኛ አለችው። በሕይወቱ ጠንቃቃ በመሆኑ ነቀፋ ያመጣብኛል ብሎ ከሚያስበው ነገር ሁሉ ራሱን ይጠብቃል። ይሁን እንጂ ስንታየሁ ከወንድሞች ከስ አለመለጠም።

እንድ ቀን «የአገልጋዮች ልዩ ስብስባ አለ» ተብሎ ይጠራል። የስንታየሁ እጮኛም ስስብሰባው ሰይ እንድትገኝ ትጠራለች። «የዘሬው ስብሰባችን ስለ ስንታየሁ ነው። እንደምታውቁት በተለይ እኛ አገልጋዮች ያለንቀፋ መራመድ አለብን። በሕይወታችን መልከም ምስክርነት ከሌለን የጌታን ሥራ እናበላሻለን» በማለት የጌታ ቤት ተቆርቋሪዎች ስመምስል የስንታየሁን ወንጀል መዘርዘር ይጀምራል።

«ስንታየሁ፣ ከብዙ ወንድሞችና እህቶች ብዙ ነቀፋ ስለ እንተ ወደ እኛ እየመጣ ነው» በማለት ንግግራቸውን ሲጀምሩ፣ ስንታየሁና እጮኛው ግራ ገብቱአቸውና ደንግጠው «ደግሞ ምን ሊወራ ይሆን» በማለት ዓይናቸውን እፍጥጠው መጠበቅ ጀመሩ።

የስብስባው መሪ ንግግሩን ስመቀጠል «የእግዚአብሔርን ቤት ስአገባቡ ስመምራት አደራ ከጌታ የተቀበልን ስለ ሆነ፣ ኃጢአት ስቤተ ክርስትያናችን እንዲስለጥን እንፈልግም። ስማያምኑት ሰዎች መበናከል መሆን እንፈስግም። ስንታየሁና እጮኛው ብዙ ጊዜ አብረው ይውሰሉ፤ አብረው ይታያሉ። ስተለይ ከእንድ ወር ስፊት ሁለቱ ብቻቸውን ከስንታየሁ ቤት ስብዙ ስዓት ቆይተው ሲወጡ እንዳንድ ከርስትያኖች ስለ

እዩአቸው «የሥጋ ግንኙነት ሰይፈጽሙ አይቀሩም» የሚል ሀሳብ በብዙዎች ዘንድ መጥቶአል። ይሄም በተለይ ከአንድ አገልጋይ የማይጠበቅ በመሆኑ ስብዙዎች መሰናክል ሆኗል።»

«ለለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲጠነቅ አያየን እኛ ኃሰፊነት ያሰብን አገልጋዮች ውስጤ ሰንሰጠ፤ ዝም ማለት አንችልም። ለለሆነም ከዛሬ ጀምሮ ሰንታየሁ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ምንም ዓይነት አገልግሎት አንደይሰጥ ሰልተወሰነ ጊዜ ተወግደአል። ሰንታየሁ የሚሰጠው አሰተያየት ከለ ከዚህ ሰኋላ እንዲናገር እድል አለጠየሰሁ» ይሰል።

ስንታየሁም ሰመደነቅና በመገረም፤ ከዚህ በፊት ደጋግመው እርሱ በሴለበት ብዙ ስብሰባዎች እድርገው የወሰኑትን ውሰኔ የማስለወጥ ኃይል እንደ ሌለው ሰለተረደ «ምንም ጥያቄና አስተያየት የለኝም፤ እግዚአብሔር ይሰጥልኝ» ብሎ ትቶአቸው ወጣ።

ስንታየሁ ወደ ቤቱ እሮኛውን ይዘ ሮጠ። ልክ እቤቱ እንደ ደረሰ ከወለሱ ሳይ ተደፍቶ ሰቅሰቅ እያለ በማልቀስ «ጌታ ሆይ፤ ያለ አግበብ ሲፈረድብኝ፤ ያለ አግበብ ስሜን ሰጭቃ ሲለውሱት፤ ያለ አግበብ ከአገልግሎቴ ሲያበሩርኝ ዝም ትሰለህ? የት ነው ያለኸው? አትፈርድም? ትከክለኛ ፍርድህ የት ነው? ያለ ነቀፋ ለመኖር ምን ያህል እራሴን በንጽህና አንደጠበቅሁ አንተ ታውቃለህ! ታዲያ ውሸት ሲሰለጥንና እውነት ሰትደሰቅ አንተ የእውንት ጌታ የሆንክ ዝም ለምን ትሰለህ?» በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ሰንታየሁ ሙግቱን ይቀጥሳል።

የሰንታየሁን አይነት መበደል ደርስባቸው፤ ልባቸው ተሰብሮ፤ ከአገልግሎት ተባረው የቀሩ ስንቶች ይሆኑ? ብዙዎች ታግሰው የቆዩ፤ በተዋረዱበት አከባቢ ሲከበሩ፤ መታገሰ ያቃታቸው ግን ከከርስትያን ሕብረት ሸሽተው ወደ ዓለም የገቡ እንደ ማይጠፉ እንገምታለን።

ብዙ ነገር ታግሰን መኖር እንችሳለን። ያለ አግበብ ሰንነቀፍ፤ ሲፈረድብን ግን ያን ችሎ መኖር በጣም ይከብድብናል። ለበጎ ይሆናል ብለን ያደረግነው፤ የተናገርነው ወደ ከፉት ተጠምዝዘና ተሰውሮ ስናይ ውሰጣችን ይደማል። ብዙ ጊዜ መከሰከያ የለንም፤ ሰሚ የለንም። የሚሸሸን እንጂ የሚቀርበን አይገኝም። ያም ይበልጥ ይጎዳናል።

እኔና በሰቤቴ በዚህ ሕይወት አልፈናል። አሁንም በውስጡ

እያለፍን ነው። ወደ ፊትም እናልፍበታለን። ያለፈውን ጊዜ ይፈታዋል፤ በፍሬያችን ይፈረድብናል ወይንም ይፈረድልናል በማለት ትተነዋል። ጊዜ መልሰችንን ሰጠን። ሰአሁኑ ወቅት የምናልፍበትንም እንደ ጥንቱ «ጊዜ ይሰየዋል» ብለን በትዕግሥት ለማለፍ እየጠበቅን ነው።

ከዚህ በፊት ሞርደን ያለፈው ፍርድ፤ ከጌታ ጋር እጣብቆን ወደ እርሱ ወርውሮን ሄደ። ያ ብቻ አይደለም። ልባችንን ሩህሩህ አደረገው። የሌሎች መድማት፤ የሌሎች መገፋት በቀሰሱ እንዲስማን ሆነ። ያለ አግበብ ሲገፉ፤ ያለ አግበብ ሲነቀፉ፤ ከአገልግሎታቸው ሲበረሩ፤ ያቀፉአቸው ገፍተው ሲያበርሩአቸው፤ ሲደሙ፤ ሲቆስሱ ሰናይ በቀለሱ ይግበን ጀመር። ሕመማቸውን፤ ሕመማችን አድርገን መውሰድ ተማርን። ድንጋይ እንስተን ከምንወረውርባቸው ይልቅ አብረናቸው ሰድንጋይ መወገርን መረጥን። ከአብዳሮች ጋር ከመተባበር ይልቅ፤ ከሚሰደዱት ጋር መለደድን መረጥን። ይህን ዓይነት ሰሚት እንዲሰማን የሆንነው በውሰጡ ስለ አለፍንበት ብቻ ነው።

ያለ አግበብ ተፈርደባቸውና ተነቅፈው ሲባረሩ ስናይ «አይዘአችሁ» ማለትን ተማርን። የአገልግሎት ሰር የተዘጋባቸውን ሌላ የአገልግሎት ሰር ከፍቶ መስጠትን መረጥን። ይህም የርሀራሄ ተግባራችን ብዙዎችን አስቆጣቸው። የድንጋያቸው እወራወር አቅጣጫውን ለውጦ ወደ እኛ እንዲመጣ አደረጉት። «እነርሱ አመጸኞችን ያቅፉሱ። ቤተ ከርስትያን ዲሲፕሊን ከምታደርጋቸው ጋር ይተባበራሱ። የኃጢአተኞች ተባባሪዎች ናቸው» አሉን። ይሁን እንጂ ከሚደሙት ጋር ስመደማት፤ ከሚያለቅሱት ጋር ማልቀስ፤ ከተባረሩት ጋር መባረር ሰምድር ዋጋ ባይኖረውም፤ በሰማይ ግን ዋጋው ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ችለናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ አግበብ የተሰደደና የተባረረ ለው ቢኖር ዳዊት ነው። ዳዊት ገና የበግ እረኛ ሰሰ ሰሙኤል ከሜዳ አስመጥቶ፤ እራሱን በዘይት ቀብቶ የእሥራኤል ንጉሥ እንደሚሆን ሰእርይ ቤተሰብ ገልጾ ነበር። ይሁን እንጂ ንጉሥ ለመሆን ያለ አግበብ መገፋትንና መሰደድን መማር አለፈሰጊው ሆነ።

ንጉሥ ሰእል በራሱ እምነት ሰላልነበረው፤ እውቀትና ኃይል አለቸው ብሎ የሚገምታቸው ሰዎች ሰአከባቢው ሲገኙ ይቁነጠነጣል፤ ይፈራል፤ ጭንቀት ይሰማዋል። ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ወገን የሆነውን ጎልያድን ድል መትቶና የእሥረኤል ጦር ሠራዊት እሸንፎ ወደ

ከተማው ሲገቡ፤ ሴቶች በዕልልታ ተቀበሏቸው። ሰአልንና ዳዊትን ሲያሞግሱ፤ «ሰአል ሺ፣ ዳዊት ግን 10 ሺ ገደለ» አሉ (መ ሰሙኤል ቀ 18፤7)።

ይሄ ምስጋና ሰአልን አበሰጨው። ያበሰጨው ዳዊት በ9ሺ ስለ በለጠው ሰይሆን፤ ለእርሱ የሚሆነውን ምስጋናና ከብር ለዳዊት የተሰጠው በመሆ ኑ ነው። ያለ አግበብም በዳዊት ሰይ ፈረደበት። «ዳዊት ዙፋ ኔን ሊነጥቀኝ ነው» ሲል አሰበ። «ሰአልም እጅግ ተቆጣ ይህም ነገር አሰከፋው፤ እርሱም «ለዳዊት አልፍ ሰጡት ለእኔ ግን ሺ ብቻ ሰጡኝ፤ ከመንግሥት በቀር ምን ቀረበት» አለ። ከዚህም ቀን ጀምሮ ሰአል ዳዊትን ተመ ቀኝቶ ተመለከተው።» (ሰሙ ቀ 18፤8–9)።

ሰአል ነገሩን ሲያጋንን እንመልከት። ዳዊት ለመንግሥ እይደለም ወደ ጦር ሜዳ የሄደው። አንድ ቀን ምግብ ለወንድሞቹ ለማድረስ ሲሄድ ጎልያድ ሲፎክር አገኘውና በእግዚአብሔር ኃይልን ተቀብሎ ገደለው። ከዚያን ቀን ጀምሮ ዳዊት ለሰአል ቅርብ ሆነ። ለበጎ ያደረገው ተግባር፤ በክፉ ተጠምዝዘበት ሰአል «ዳዊት ዙፋ ኔን ከእ ኔ ነጥቶ ሊወስድ ነው» አለው።

ለብዙ ጊዜ ዳዊት ከሰአል ሰይፍ ለማምለጥ ሰደተኛ ሆኖ ኖረ። ሰአል አውሬ እንደሚያሰድድ ዳዊትን አሰደደው። ቅናት በነደደው ሰው መታደንን የመሰለ መራራ ነገር የለም። ብዙ የመጽሐፍ ቅዱሰ ሊቃውንት «መዝሙረ ዳዊት 140 ሰዚህ ምክንያት የተፃፈ ነው» ይላሉ።

«እቤቱ ከከፋ ሰው አድነኝ፤ በልባቸውም ከፋ ከአሰቡ፤ ከአመጸኞች ሰዎች ጠብቀኝ፤ ቀኑን ሁሉ ለሰልፍ ይከማቻሉ። ምላሰቸውን እንደ እባብ፤ ከከንፈራቸው በታች የእፉኝት መርዝ ነው፤ እቤቱ ከኃጢአተኞች ጠብቀኝ» አለ (መዝ 140 1–4)። ዳዊት የአሰዳጆቹ ክፋትና ተንኮል ምን ያህል ረቂቅ እንደ ሆነ ጥሩ አድረጎ ገልጾታል። ምላሰቸው እንደ እባብ የሚናደፍ፤ ከከንፈራቸውም በታች የእፉኝት መርዝ እንደለበቸው ይገልፃል። እንደ እነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች በሰው አዕምሮ ውሰጥ ከፋ ነገርን ይረጫሉ።

ያለ አግበብ ተነሰተው የሚያሰድዱንን፤ ከፋ ነገር የሚያሰወሩብንን፤ ምን ማድረግ እንችሰን? ዳዊት እንደለው እንለለን። ዳዊት «እግዚአብሔርንም አንተ አምለኬ ነህ፤ የልመናዩን ቃል አቤቱ

አድምጥ አልሁት» (መዝ 140፤6)። ዳዊት ማለት የፈለገው «ጌታ ሆይ ያንን ሰው አንተ እራሰህ ያዝልኝ፤ እኔ አልችልም» ለማለት ነው። እኛም ራሰችን በመዋጋት ፈንታ «እስበ አንተ ተዋጋልኝ» እንበለው። የፈርእን ሠራዊት የእሥራኤልን ሕዝብ አሰደ ለመያዝ ሲሞከር፤ ሙሴ ሕዘቡን ያጽናናበት ቃል «እግዚአብሔር ሰለ አናንተ ይዋጋል፤ አናንተ ዝም ትሰለችሁ» አለቸው። (ዘዳግም 14፤14)።

በመገፋት ውሰጥ አድገት አለ። በዚያ ውሰጥ እግዚአብሔር ለእኛ ሊዋጋና ጠበቃ ሲሆን እናየዋለን። የከሰሸችን ምላሰ እኛን ለማጥፋት ያለ እንቅልፍ ሲያድር እኛ ግን «ጌታ ይዋጋልኛል፤ መልሰ ይሰጥልኛል» በማለት የጸጥታና የሰላም እንቅልፍ እንተኛለን።

ያለ አግበብ የሚገፋን፤ የሚያሰጨንቁን፤ የሚያሰዝኑን አሉ? ለእግዚአብሔር እንንገረው። ወላጆች አንደ ሌላቸው ልጆች ሆነን አይሰማን። ለአባታችን እንንገረው። እርሱ አሰፈለጊውን እርምጃ ይወሰዳል። የታወቀው ሊ ኤሰ ሉዊሰ እንዲህ አለ። «በደሰታችን ወቅት እግዚአብሔር ለሰለስ በለ ድምጽ በሕሰናችን እማከኝነት በቀስታ ይናገረናል። በመከራችን ጊዜ ግን፤ ጮሆ ይቀሰ ቅሰናል። «መከራ» እግዚአብሔር ሲጠራው ለማይሰማ፤ ደንቆሮ ጀሮ ሰለው ሰው መቀሰቀሻ የድምጽ ማጉያ ነው» አለ።

መነቀፍ ምን ያህል ይጎደን ይሆን? የአሜሪከ ፕሬዚዳንት የነበሩት ሀሪ ትሩማን «ሙቀቱን ከፈራህ ወጥ ቤት አትግበ» ሲሉ ተናግሩ። በትልቁ ከሰብከ፤ በትልቁ ለመሥራትና ለማደግ ከተመኘህ፤ የሚደርሰብህን ነቀፌታ ለመቀበል ደረትህን ሰፋ አድርገህ ጠብቅ።

አንድ ጸሐፊ ሁለት ዓይነት ሰዎች በዓለም ላይ ይገኛሉ አሉ። 1ኛው፤ አናጢ (ገንቢ) ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ «ነቃፊ» ነው። አናጢው (ገንቢው) ሁልጊዜ አዲሰ ነገርን ይፈጥራል፤ ይለውጣል፤ ይጠግናል፤ ያቆነጃል። ዓለም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ያሰፈልጋታል፤ ለሰው ልጆች እንዲህ ዓይነቱ ሰው በረከት ነው።

ነቃፊው ደግሞ፤ «ሰው–በሰ» ሲሆን፤ በሰዎች ድከም ፈንጠዝያ የሚያደርግ ነው። ነቃፊ፤ በራሱ ለህተት የታሠረ ሰው ነው። ነቃፊ፤ የሚያወራው፤ (የሚያጋንነው) የራሱን ድከምና የችሎታውን ማነሰ ነው።

አንድ መክሊት ብቻ ያለው ሰው፤ ያቺው ያለችው መክሊት ምን

እንደሆነ ሲጠየቅ የሰጠው መልስ፤ «ሌሎችን መንቀፍ ነው» አለ። ጠያቂውም ሲመልስ «እንዲህ ከሆነማ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ መክሲት እንደነበረውና ወደደ እንደቀበረው ሰው፤ አንተም ይህን መክሲትህን ውሰድና ቅበር» አለው።

በእረግመዱ ፍጹምና ንጹህ የሆነው ክርስቶስ እንኳ ከመነቀፍ ነፃ አልነበረም። በዚያም ብዙዎቻችን እንጽናናለን። «ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ፤ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁአን ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታሳቅ ነውና ደስ ይበላችሁ። ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና» (ማቴ 5፤11–12)።

ስንነቀፍ፤ ሳንበረግግ፤ የምንሠራውን በጎ የሆነውን ሥራ በመሥራት ወደ ፊት በመሸምጠጥ እንቀጥላለን? ወይንስ እንሠራ የነበረውን ሥራ እርግፍ አድርገን ጥለን አንድ ጉበጉሽ ውስጥ ገብተን እንደበቃለን? ወይንስ የምንሠራውን ሥራ ቀድሞ ከነበረው የበለጠ በመሥራት ተቃዋሚዎቻችን ፍሬያችንን የበለጠ እንዲያዩ እናደርጋለን?

አንደንድ ሰዎች ትንሽ ወቀሳ ሲደርስባቸው፤ የሚይዙትና የሚጨብጡት ጠፍቶአቸው ይደነግጣሉ። ለበዙ ጊዜ እህል አልበላ ይላቸዋል፤ ማጥናት፤ መሥራትና መተኛት ያቅታቸዋል።

ሰው በሕይወቱ የወጠነውን ነገር ከግቡ ለማድረስ ከሚያስፈልጉት ነገሮች መካከል እንደኛው፤ ነቀፋ ቢደርስበት የማይደናገጥና የማይደናበር መሆን ነው። ያለ አግባብ ስንነቀፍ፤ ያለ አግባብ ሰዎች ስለ እኛ ከፈ እየተናገሩ ሲያጠቁን ሲሞክሩ «ጌታ ሆይ ለምን ዝም አልከ? የት አለህ? እንተ መፍረድህን አቁመሃል?» ብለን የምሬት ቃል ማሰማታችን ግልጽ ነው።

ነቀፋ ሲደርስባቸው ቶሎ ተሰባብረው የሚወድቁ ሰዎች አሉ። በነቀፋታ ውስጥ እንዴት ድል አድርገው እንደሚወጡ አያውቁም። ከክፉ ነገር ውስጥ በጎ የሆነውን ነገር የማግኘት ችሎታ የሰቸውም። ነቀፋ ወደ በጎ ነገር እንዲለወጥ በመትጋት ፈንታ ስሜታቸው ይረበሻል፤ ተሸናፊዎችና እንዲሁም ለራሳቸው የሚያዝኑና የሚያሰቅሱ ይሆናሉ።

ያለ አግባብ መነቀፍ ሲደርስብን ምን እናድርግ?

1) ነቀፋ ሲደርስብን፤ «የተነቀፍኩበት ነገር እውነትነት አለው? በእርግጥ መነቀፍ የገባኝል? ከዚህ ውስጥ ምን ትምህርት አገኝበታለሁ?» በማለት ረጋ ብለን፤ ሳንደናገጥና ሳንረበሽ ራሳችንን እንጠይቅ። እርግጥ ነው፤ ምንም ያህል ሰዎች በቅናትና በምቀኝነት ተነሳስተው ስማችንን ሲያጠፉ የሰነዘሩብን መሠ ኑን ብናውቅም፤ በጎ ነገርን እንማርበታለን።

2) ነቀፋ ሲደርስብን፤ ነቀፋው ከየት፤ ከማን እንደመጣ በጥንቃቄ እንመርምር። ብዙ ጊዜ ሳንፈጅ ነቀፋታው የተሰነዘረው ይህን ያህል ከእኛ በተሸለ ሰው እንደልሆነ እንረዳለን። ያንንም ስናውቅ ነቃፊው የራሱን ድክም ማውራቱ መሆ ኑን እንገነዘበለን።

«ሳይኮሎጂ ኢንድ ሞራል» በሚለው መጽሐፉ፤ ሀድፊልድ የተባለው ሰው «በሌሳው ሳይ የነቀፋታ ቃል የሚያወራ፤ የራሱን ድክምና በሀተት ያውጃል» አለ። ሌሳውን የሚነቅፍ፤ ነቀፋታው፤ መስተዋት ሆኖ የራሱን ደክማ ወገን ያሳያል። ኢየሱስም የተናገረው ይህንን ነው። «እንዲይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱት ፍርድ ይፈረድባችሂል፤ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችሂል፤ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ በለምን ትመለከታለህ? ወይም ወንድምህን ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆ በዓይንህ ምሰሶ አለ። እንተ ጎበዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ፤ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ» (ማቴ 7፤ 1–5)።

3) አንዱ እኛን ዝቅ ሲያደርገን፤ ሲያሳንሰንና ሲያንቋሽሸን ሲሞክር ሰናይ፤ እኛን በራሱ መጠን (size) ሊወስነን መሞከሩ እንደሆነ እንገንዘብ። ሳይሠራ ተቀምጦ የሚተቸን፤ እኛም እንደ እርሱ እንዳንሠራ ለማድረግ እንደ ሆነ እንረዳ። እንዲህ ዓይነቱ ሰው፤ የሌሎችን ስህተትና ደክም በመልቀም ራሱን የሚያሰጪንቅ ደክማ ሰው መሆ ኑን እንገንዘብ።

4) ምንም ዓይነት ነቀፋታም ቢሆን ወደ ኋላ ሳንል የምንችለውን ያህል በርትተን እንሥራ። አግዚአብሔር ሲያበጀን በእንደዚህ ዓይነት ቹግር ውስጥ ሁሉ አሸንፈን እንድንወጣ ኃይልን በውስጣችን አድርጎ ነው። በነቃፊዎች ፊት ራሳችንን ለመከላከልና አቋማችንን ለማበረዳት ተጪንቀን እንርበትበት። ጊዜና ሁኔታ እንዲሁም ጌታ እራሱ ይፈታዋል ብለን እንጠብቅ።

ነቀፋታን ከሚያራግቡ ሰዎች መካከል እንዱ የሚነቀፈውን

ሰው፣ «ለሚነቅፉህ ሰዎች መልስ አትሰጥም እንዴ?» ሲል ጠየቀው። ተነቃፊው ሲመልስ፣ «በጊዜው» አለው። «መቼ? እንዴት?» ሲል መልዕ ጠየቀ። «ሰወቅቱ፣ ፍሬው ሲታይ» ብሎ መለሰለት ይባላል። ሰንነቀፍ ወደ ፊት እንቀጥል፤ እንሸምጥጥ እንጂ እንደናገጥ።

3

በብቸኝነት ስንሰቃይ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?

በሎሰ እንጀለሰ ከተማ ውስጥ በአንድ ቴሌቭዥን ፕሮግራም፣ ሰዎች በጣም የሚረብሻቸው ድምጽ ምን እንደሆነ ጥያቄ ቀርቦለቸው ብዙዎች የተለያየ መልስ ሰጡ። እንዲ ሲመልስ «ከሥራ መልስ፣ ወደ አሥራ አንድ ሰዓት ገደማ የሚኖረው የትራፊክ ድምጽ ይረብሸኛል» አለ።

ቤቷ አይሮፕላን ማረፊያ አጠገብ የሆነችዋ አንዲት ሴት ደግሞ «አይሮፕላን ሲነሳና ሲያርፍ የሚያሰማው ድምጽ አንገሽግሾኛል» አለች። ይህን የመሰሉ ብዙ የተለያዩ አስተያየቶች ከተለያዩ ሰዎች ቀሰጥተዋል። አንድ ወጣት ብቻ ግን ከብዙዎች ፍጹም የተለየ መልስ ሰጠ። «በሕይወቴ በጣም የሚረብሸኝ፣ ፍጹም ልታገሰው የማልችለው ነገር ቢኖር፣ ብቸኝነትን ነው» አለ።

ብዙዎች በሰው መሃል እየኖሩ በብቸኝነት የሚሰቃዩ አሉ። በዙሪያቸው ብዙ ሁከታና ድምጽ አለ። ይሁን እንጂ የእነርሱ ሕይወት ፍጹም ጸጥታና ዝምታ የበዛበት ሕይወት ነው። የሚያናግራቸውና

የሚያናግሩት የሰቸውም። በሌሳ በኩል ደግሞ የሚያናግራቸው ቢኖርም፣ ውስጣዊ የሆነውን ስሜታቸውን የሚገልጹለትና የሚገልጽሳቸው የለም። በሁለቱም አቅጣጫ ያሉ ሰዎች በብቸኝነት ይሰቃያሉ።

ዳዊት በብቸኝነት በሚሰቃይበት ጊዜ እንዲህ አለ «በሰገነት እንደሚኖር ብቸኛ ድንቢጥ ሆኑሁ። ጠሳቶቼ ሁልጊዜ ይሰቁብኛል። የሚያሰድዱኝም ተማማሉብኝ» (መዝ 102፣7-8)። ኤልያስም በብቸኝነት ሕይወት ውስጥ ሲያልፍ በዋሸው ውስጥ ተቀምጦ «የእሥራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፣ መሰዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፣ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋል፤ እኔም ብቻዬን ቀርቼአለሁ፤ ነፍሲንም ሊወስዷት ይሻሉ» (መ ነገሥት ቀ 19፣10) ሲል፣ እግዚአብሔርም ኤልያስ ብቻውን እንደልቀረ ሲገልጽሰት «ሰበት ሺ ሰዎች ለእኔ አበቀራለሁ» አለው።

የብቸኝነት ዓይነቶች

1) <u>ከሰው ተለይቶ በመኖር የሚመጣ ብቸኝነት አለ።</u>

ሰው ወደም ሆነ ሰይወድ ብቻውን መሆን ይችላል። በጫካ ወይንም በተራራ፣ ከሰው ሁሉ ተለይቶ ለብቻው የሚኖር ሰው አለ።

2) <u>በሕዝብ መካከል እየኖሩ የሚሰማ ብቸኝነት አለ።</u>

በዙሪያቸው ብዙ ሰዎች ይመላለሳሉ፤ በአካባቢያቸው የሚኖሩ ሰዎች አሉ። ይሁን እንጂ የተቀራረበ ግንኙነት ከማንም ሰው ጋር ሰይኖራቸው ብቸኞች ሆነው የሚኖሩ ሰዎች አሉ።

3) <u>የመከራ ብቸኝነት አለ።</u>

በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሁሉ ጤነኞች ሆነው እንዱ ብቻ በተለየ ሕመም የሚሰቃይ ይኖራል። ስለ ደረሰበት ሕመም የሚያዝኑለት ሰዎች ይኑሩ እንጂ፣ አብረውት የሕሙን በቃይ በለማይቀምሱ፣ በሕመማቸው ብቸኞች የሆኑ አሉ።

4) <u>የህዘን ብቸኝነት አለ።</u>

በህዘን ልቡ የተሰበረ ሰው፣ እርሱ የሚሰማውን ዓይነት በሜት ሌሎች ስለማይሰማቸው በሃዘናቸው ብቸኞች ይሆናሉ። ህዘን የእንድ ሰው ብቻ ውስጣዊ ልምምድ ነው።

5) <u>በዋጋቢስነት በሜት የሚመጣ ብቸኝነት አለ።</u>

«የማልረባ ነኝ ዋጋ ቢስ ነኝ» የሚል ሰው ራሱን ገለል ስለሚያደረግ፣ ብቸኝነት ያጠቃዋል። ኤልያስ በዚህ ዓይነቱ ብቸኝነት ተሰቃይቷል። «ጌታ ሆይ እኔ ከአሰቶቼ አልበልጥምና ግደለኝ» ብሎ ቢጸልይ፣ በብቸኝነት መሰቃየቱን ያሳያል።

6) <u>በአበተሰሰብ ልዩነት የሚመጣ ብቸኝነት አለ።</u>

አበተሰሰቡ ከሰው ልዩ የሆነ ሰው አለ። በአከባቢው ካሉት ሰዎች ጋር፣ እንደሚያበቡትና እንደሚያደርጉት ማድረግ ስለማይችል ብቸኛ ይሆናል። አበተሰሰቦችን ከሕብረተሰቡ የተለየ በመሆኑ ይከንኑናል፤ ይፈርዱብናል። በዚህ የተነሳ የብቸኝነት በሜት ያጠቃናል።

7) <u>በምናደርገው ውሳኔ ምክንያት የሚመጣ ብቸኝነት አለ።</u>

ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ፣ «ናቡከደናጾር ለአቆመው ምበል እንሰግድም» በማለት ውሳኔያቸውን አበታወቁ። እምቢልታው ሲነፋ፣ ከበሮው ሲመታ፣ በዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ ተደፍቶ ሲሰግድ፣ ሰበቱ ብቻ ተለይተው ሰይሰግዱ ቆሙ። በወሰኑት ውሳኔ ምክንያት ብቸኞች ሆኑ።

በሌሳ በኩል ደግሞ ሌሳ ሰው ሊወስንልን የማይችለው እኛው እራሳችን ብቻ ከውሳኔ መድረስ የሚገበን ጊዜ አለ። በዚያ ሁኔታ ሳይ ሰሰን በእርግጥም ሰቸኞች ነን። ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ብቸኝነት ጥሩ ልምምድ ነው።

ሰብቻ መሆንና፣ ብቸኝነት ፍጹም የተለያዩ ናቸው። ብዙ ሰዎች ለብቻቸው ሲሆኑ በጣም ደስ የሚሳቸው አሉ። የብቸኝነት በሜት የሚሰማቸው ሰዎች ግን ደስተኛ የሚሆኑበት ጊዜ የለም።

የእሥራኤል ሕዝብ በስደት በነበረበት ጊዜ፣ ሰሰርያው በኢሳያስ በኩል «እጽናኑ፤ ሕዝቤን እጽናኑት» ሲል ትዕዛዝ ሰጠ። የእግዚአብሔር

ሕዝብ ያሰ ቤት፣ ያሰ አገር ልቡ ሰሀዘን ተሰብሮ የሚኖርበት ዘመን ነበር። ዕድሚያቸውን ሰምርከ፣ ነፃነት ሰማጣት እንዲኖሩ የተገደዱበት፣ ሰኃጢአታቸው ምከንያት እግዚአብሔር ፈርደበቸው ይመስሳቸው ነበር። የሰደሰኝነትና ተሰፋ የመቁረጥ ሰሜት ይሰማቸው ነበር። ሰዚህ ነው «አጸና ኑ፣ ሕዝቤን አጽና ኑ» ሲል እግዚአብሔር የተናገረው።

ማንኛውም ሰው በሕይወቱ ብቸኝነት የሚሰማው ጊዜ ይኖራል። ሰአንድ ቤት ውስጥ ከብዙ ሰው ጋር እየኖረ ብቸኝነት ሊያጠቃው ይችሳል። ማንኛውም ሰው ሰድንገተኛ በሽታ ሲሰቃይ፣ ሥራ ሲያጣ፣ የሚወደውን በሞት ሲለይ፣ አጥጋቢ ባልሆነ ምከንያት ሰሌሳው ሰው ሲከዳ፣ ድጋፍ ፈልጎ፣ ድጋፍ ሲያጣ፣ የብቸኝነት ስሜት ይሰማዋል። ደከሞን ማረፊያ ስናጣ፣ የውስጥ ጩኸታችንን ሰማሰማት ፈልገን ሰሚ ሰናጣ፣ መግለጽ የማንችለው ውሰጣዊ እሰመመቸት ሲሰማን፣ በብቸኝነት እንሰቃያለን። በዚህ ጊዜ ድምጻችንን ከፍ አድርገን ወደ ጌታ እየተጣራን «በብቸኝነት ሰሰቃይ ሰምን ዝም ትሰለህ?» ብለን እንጠይቀዋለን።

ብቸኝነት ሲሰማን የሚያጽናናን ሰው መፈለጋችን ኃጢአት ወይንም ድከመት አይደለም። ሌሳውን ማጽናናት ጥሩ እንደሆነው ሁሉ፣ እኛም ሰንጽናና በጎ ነው። ብርቱዎች መሰለን መታየቱ መልከም ነው፤ ይሁን እንጂ ድከም እንደሰብን ማሰየቱ ደግሞ ሰዚያው ልክ መልከም ነው። ማናችንም ብንሆን ሰሕይወታችን መጽናናትን ሰጣም የምንፈልግበት ጊዜ አለ። መጽናናት መቻል ማስት የሚጠነቀቅልን አምሳክ በዙሪያችን መኖሩን አምኖ መቀበል ማስት ነው። እግዚአብሔር ዘራም ቢሆን «አጽና ኑ፣ ሕዝቤን አጽና ኑ» ይሳል።

አንዳንድ ጊዜ የሕይወትን ጉዘ ብቻችንን መጊዝ የሚያሰፈልግበት ጊዜ አለ። አንዳንድ የሕይወት መንገድ ከአንድ ሰው በሰተቀር አያሳኬድም። እኛ ብቻ አንድንሸከመው የሚያሰፈልግ ሸክም አለ። እኛ ብቻ ልንቀበሰው የሚገባ ሀዘን አለ፤ እኛ ብቻ ልንወስነው የሚገባ ውሳኔ አለ። ይህን ዓይነት ብቸኝነት ሰበጎ ስለሆነ በብቸኝነታችን ተማረን በእግዚአብሔር ሳይ የወቀሳ ድምጽ እናሰማ።

እየሱስ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ሰበረሀ ተመሳስሰ። መጽሐፍ ቅዱስ ሲጀምር፣ እግዚአብሔር ብቻውን እንደነበረ ይገልፃል። «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ይሳል (ዘፍ 1፣1)። መጽሐፍ ቅዱስም ሲጨርስ ዮሐንስ ሰጳጥሞስ ደሴት ብቻውን

እንደ ነበረ (ራዕይ 21፣1) ይናገራል።

ጥሩ የሆነና መጥፎ የሆነ ብቸኝነት አለ። ጥሩ ዓይነቱ ብቸኝነት ገንቢ ነው። «ሰመመለስና በማረፍ ትድናሳችሁ፤ ሰጸጥታና በመታመን ኃይል ይሆንሳችሏል» ይሳል (ኢሳ 30፣15)። ብቸኛ ሰንሆን እዕምሮአችን በኃይል የሚሠራበት ጊዜ አለ። ብቻችንን ሰንሆን ከራሳችን ጋር መነጋገር እንችሳለን። ብቻችንን ሰንሆን እግዚአብሔር ሲናገረን ይችሳል።

መጥፎው ብቸኝነት ደግሞ ከዚህ ይሰያል። ህዘንን ሰውሰጣችን ይቀሰ ቅሰል። ስሜታችን ሰብርብሩ ይወጣል። የአእምሮና የመንፈስ ጭንቀት ያደርሰብናል። እራሳችንን ዋጋ ቢስ አድርገን እንድንገምት ያደርገናል። ይህን ዓይነት የብቸኝነት ስሜት አጥፊ ስለሆነ መጠንቀቅ ይገባናል።

አንዳንድ ጊዜ ከምንወዳቸው ሰዎች ስመለየት ፈቃደኞች መሆን ያሰፈልገናል። «ምን ዓይነት ሰው ነኝ? ምን ዓይነት ሰው መሆን ያሰፈልገኛል» ሰማለት ራሳችንን መጠየቅ የሚያሰፈልገን ጊዜ ይኖራል።

ከሰው ጋር ስመቀሳቀል ጥማት አለን

ታሰረው ከወህኒ ቤት የወጡ ሰዎች፣ ሕይወታቸውን በአዲስ ምዕራፍ ስመጀመር ይፈልጋሉ። ትልቁ ጥማታቸው በሕብረተሰቡ መካከል የሚቀበሳቸውን ሰው ማግኘት ነው። ይህ ጥማት የእነርሱ ብቻ ሳይሆን የብዙዎቻችን ፍሳጎት ነው። ሰዎች እንዲቀበሉን፣ እንዲያደንቁን ከሕብረታቸው እንዲቀሳቅሉን እንፈልጋለን። በዕድሜ ወጣቶች ሳለን ከሚያሰፈራን ነገሮች መካከል ትልቁ ጌደኛ አልበ መሆንን ነበር። በዕድሜ ሰንጎለምመም ሰሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀበይነት ማግኘትን እንጠማለን። ብቻ መሆንን፣ መተውን የሚፈልግ ሰው የለም። በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀበይነት ስማግኘት መፈለግ ኃጢአት ወይንም ድከመት አይደለም።

ብዙ ጊዜ ብዙ ሰዎች ተቀበይነትን ስማግኘት ብዙ ይደክማሉ፤ ልዩ ልዩ ስጦታን ይሰጣሉ። የሚያሰዝነው፣ አንዳንዶቹ ተቀበይነትን ስማግኘት ብቻ ሲሉ የእምነት ፍልሰፍናቸውንና አቋማቸውን ይለውጣሉ (ይከዳሉ)። ተቀበይነት ያጡ የሚመስሳቸው ጥቂቶች ሰዎች ቶሎ ተሰፋ ይቆርጣሉ፤ የብቸኝነት ሰሜትም ይሰማቸዋል። እንዲሁም ሰራሳቸው

የሚያዝኑና የሚያስቅሱ ይሆናሉ።

እውነተኞች ስዎች ስመሆን ብቻችንንም ሆነን፣ እንዲሁም በስዎች ፊት እውነትን እንያዝ ። ማድረግ የምንችስውንና የማንችስውን፣ መሆን የምንችስውንና የማንችስውን መገመት ይገበናል። ማድረግ ከምንችስው በስይ ስማድረግ እንሞክር። ካልቻልንም ለስመቻለችንን መሸሸግ አይገበንም። የትኛውም ሕብረተስብ ወስጥ ብንሆን ተፈጥሮአችንን ስንስቅ የሆነውን ሆነን መቅረቡ በጎ ነው። ትንሽም ሆነ ትልቅ፣ የራስችን የሆነ ልዩ ተስጥእ ያስን መሆናችንን ተረድተን ልበችን በመስጋና ይሞስ። እግዚአብሔር ሲፈጥረን እራስችንን እንድንሆን ነው እንጂ ሌለ ስው እድርጎ ለልፈጠረንም።

በስው ሕይወት ትልቁ ጉዳት፣ ሰስበት ሕብረተስብ ወይም ለክባቢ ተቀባይነት ያጣ እንደሆነ ነው። በሥጋው ሕመም ያስበት ስው፣ ሀዘንተኛውም፣ መሸነፍ የደረስበት፣ ያዘነና የተበሳጨም መታገስ ይኖራል። ሰስው ተገፍቶ (ችስ ተብሎ) መኖር ግን እጅግ በጣም ከባድ ነው። ይህ መገፋት በሀብታሙም ሆነ በድሀውም፣ ከዚህ በፊት ተከብረው የኖሩም ቢሆኑ እንድ ቀን ሲደርስባቸው ይችስል።

በስው የተገፋ፣ ችስ የተባሉ፣ ምንም እንኳን እራስቸውን ምንም እንደልደረሰባቸው ቢሸፍኑም፣ በብቸኝነት የሚኖሩ ብዙ አሉ። በስው መገፋት ወይንም ችስ መባል ነፍስንና መንፈስን አክስ ስንክስ አድርጎ የሚያጠፋ በሽታ ነው። ይህ ህመም እንደንደቹን ራስቸውን እንዲገድሉ፣ እንዲያብዱና ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል።

እንደንደቻችን መገፋትና ችስ መባልን ያደረስነው በገዛ እጃችን እኛው እራስችን እንሆናስን። በሕይወታችን ከዳረግናቸው ነገሮች መካከል እንደልነበረ የማጥፊት ዕድል ቢስጠን የትኛውን እናጠፋስን? ስሚስው ጥያቄ እንድ ስው ሲመልስ «ከዚህ በፊት ስለ ሰው የስጠሁት መጥፎ አስተያየት» ይሆን ነበር እስ። ምክንያቱንም ሲያስረዳ ከዚህ በፊት ስስ ሰው የስጠው መጥፎ አስተያየት ምን ያህል እንደስጪ ነቀውና መልስ እንደጎደው ገስጸ።

በተፈጥሮአቸው እንደንድ ልዩ የሆኑ ሰዎች አሉ። መገፋትንና ችላ መባልን ይፈልገሉ። ሰምን እንደሆነ ባይታወቅም፣ ሲታመሙ ደስ የሚላቸው፣ በሌሎች ስዎች ስደት ሲደርስባቸው ደስ የሚስቸው ስዎች አሉ። እንደ እነዚህ ያሉ ስዎች ችስ መባልን የሚያመጡት ራስቸው

ናቸው።

ተፈጥሮአችን፣ አስተሳሰባችንና እምነታችን ልዩ በመሆኑ፣ በሌሎች የማንፈስግ መሆናችንን አውቀን እንደ እውነት መቀበል አስብን። በዚህ ልዩነታችን ምክንያት አስመፈስግን እናስወግደለን ብንል፣ እራስችንን መልስን መጉዳታችን ይሆናል። አጥበቀን ስያዝነው እምነታችንና የሕይወት ፍልስፍናችን (ፐረንስፐል) ጸንተን መቆም አስብን። ሌሎች እንዲቀበሉን ስንል ብቻ አቂማችንን መስወጥ አይገበንም።

የስው ዕምነትና አቂም የሁሉም እንድ ዓይነት አይደስም። ከሌሎች የተስየ ዕምነተና አቂም ይዘን ከተገኘን፣ ከእኛ የሚስዩት ስዎች እነርሱን ስስ አስመስልን እንዳግይቀበሉን ግልጽ ነው። በሕይወታችን መገፋትን ሰመቂቂም ከፈስግን፣ ትልቅ መድኃኒት ከተገፋት ስዎች ዘንድ መቆም ነው።

ስሜታችን በሰሀሪያችን ስይ ትልቅ አስተዋጽኦ አስው። ከሰሜታችን እንደኛው ፍርሃት ነው። በፍርሃታችን የተነሳ ብዙ ጊዜ ያጋጠመንን ዕድል አንጠቀምበትም። መልክም መስስው የማይታዩንን ሰዎች «ከፋ ሳይሆኑ አይቀሩም» በማስት ሸሽተን እንኖራስን። እኛ ብቻ ሳንሆንም እነርሱም ከእኛ ሲሸሹ እናያስን።

እንደንደቻችን በቀስሉ የምንናደድ ስዎች በመሆናችን፣ ስዎች በሀሪያችንን ሲያዩ ቶሎ ይሸሹናል። በሌስ በኩል ደግሞ ዋጋ ቢስነት በቀስሉ ስስ ሚስማን በራችንን በሌሎች ላይ ጥርቅም እድርገን እንዘጋስን።

ስው በጠበዩ ወይንም በሰሀሪው ምክንያት ብቸኛ ሊሆንም ላይሆንም ይችስል። የስው ሰሀሪ ከሁለት ይከፈስል። ይኸውም ዝምተኛና (ኢንትሮቨርት) ተናጋሪ (ኤክስትሮቨርት) ነው። ዝምተኛ (ኢንትሮቨርት) ሰሀሪ ያስው ስው በቀስሉ በህፍረት ይሸማቀቃል። መጥፎ አስተያየት ሲሰጥበት ቶሎ ራሱን ሊገልጽ ይሞክራል። በቀስሉ የሚሰቅ ሰው አይደስም። የስጋስነት ጸባይ የስውም። ሀሳቡን ሰንግገር እንደ ልቡ መግስጽ አይችልም። ከውስጌ ስመድረስ በጣም ያስቸግረዋል። ውስጌ እንኳን ቢወሰን፣ ትንሽ ስየት ያስ ነገር ሲያጋጥመው ቶሎ ውስጌውን ይሰውጣል። ስብቻው መሥራት ደስ ይስዋል። ብዙ ሰዓት በቀን እያስመ ጊዜ ይጠፋል። በቀስሉ ስሜቱ የስዋወጣል። ከእርሱ ሃሳብ ጋር ከማይሰማሙት ስዎች ጋር በቀስሉ ይጋጫል።

ዝምተኛ በህሪ ያለው ሰው (ኢንትሮቨርት) ጥሩ የሆነ ወገንም አለው። ታታሪ፣ ትጉህና ዕውነተኛ ነው። ቅን፣ ተከከለኛና ታማኝ ሰው ነው።

ንቁ በህሪ ያለው (ኤክስትሮቨርት) ሰው፣ ከብዙ ሰዎች ጋር የመተዋወቅ ችሎታ አለው። ነቀፋ ቢደርሰበት፣ በቀሰሱ ሀፍረት አየተሰማውም፣ በልቡ ውሰጥ ያለውን ሰይደብቅ አውጥቶ ይናገራል። ሰይክራከር የተባሰውን ሁሉ ይቀበላል። በቀሰሱ በዙ ወዳጆች የማፍራት ችሎታ አለው። ሌሎች ሰለ ሚሉትና ሰለ ሚያስቡት ነገር ግድ የለውም። ሰሜቱ በቀላሉ አይሰዋወጥም።

በአጠቃሰይ ዝምተኛ በህሪ ያለው ሰው (ኢንትሮቨር) እንዲታወቅና እንዲመሰገን ሲፈልግ፣ ነቁ በህሪ ያለው ሰው ደግሞ (ኤክስትሮቨርት)፣ እርዳታ እንዲጠየቅ ይፈልጋል።

ያም ሆነ ይህ፣ ሰው ሁሉ ልዩ የሆነ የራሱ በህሪና ተፈጥሮ ያሰው ነው። ስለሆነም ሌሰውን ሰማሰብ፣ በሌሰው ዘንድ ተቀባይነት ሰማግኘት ሰንል ከዕምነታችን፣ ከያዝነው የሕይወት ፍልስፍናና አመራር ትንሽም ቢሆን ፎቀቅ እንበል። የራሰችንን አቂም ሰዎች አውቀው እንዲቀበሉን ብቻ ሰይሆን፣ እኛም የሌሎችን አቂም ተረድተን ልክ እንዳሉ እንውደዳቸው። አኛ እንደ ተቀበልናቸው አነርሱም እንደሰን ይቀበሉናል።

ብዙ በቸኛ የሆኑ ሰዎች በቸኝነታቸውን ለመደበቅ ብዙ መከራና ጥረት ያደርጋሉ። ከአነዚህ መካከል እንደኛው ታዋቂ የነበረው እንግሊዘዊው ሩፐርት ብሩክ የተሰለው ሰው ነው። ይህ ሰው ከሲቨርፑል ወደ ኒው ዮርክ በመርከብ ተሰፍሮ ሰመሄድ ተነሰ። መንገደኞች ብዙ እያስቀሱ የሚሸኙአቸው ሰዎች እንዳሉአቸው ተመለከተ። አርሱ ግን እንኳን ሲያሰቅስስት ቀርቶ «ደህና ሁን» ብሎ የሚሸኘው ሰው አልነበረውም። በጣም ብቸኝነት ሰለ ተሰማው ከልቡ ሀዘን ተሰማው።

ሚስተር ብሩክ በሩቁ አንድ ልጅ ብቻውን ቆሞ አየና ሮጦ አነጋገረው። «ገንዘብ ማግኘት ትፈልጋለህ?» ብሎ ጠየቀው። ልጁም በመደሰትና በመደነቅ «አዎን!» ሲል መሰበ። «ከፈለግህ» አለው ሚስተር ብሩክ «እዚህ ጋ ቁምና እኔ ወደ መርከቧ ሰገቢና መርከቧ

መጧዝ በተጀምር እጅህን አያወዛወዝህልኝ ደህና ሁን በለኝ» አለው።

«ብቸኝነት ሲያጠቃን እግዚአብሔር ሆይ ሰምን ዝም አልከ?» በማለት በእግዚአብሔር ማማረር አይገባንም። ለሪሰችን ዘማዘን ይልቅ ለጥቅማችን ልናውለው እንችሰለን። የታወቀው አሜሪካዊ ጸሀፊ ካርል ሰንድከርግ በጽሁፉ፣ የእንደንድ ታሪካዊ ሰዎችን የህይወት አቂም በመግለጽ የብዙዎችን አዕምሮ ያደበረ ሰው ነው። ይህ ጸሀፊ በዘመናቸው ታሰሰቅ የነበሩ ሰዎች እነ ሼክስፐር፣ ሲዮናርደ ደቪንቺ፣ ቤንጃሚን ፍራንከሊን፣ አብርሃም ሲንከን፣ በሕይወታቸው ሲነማ ቤት ገብተው ፈልም እንዳሰዩ፣ ሬድዮ እንደልሰሙ፣ ቴሌቪዥን እንዳልተመለከቱ ይገልፃል። ይሁን እንጂ በሥራቸው ተደናቂዎች፣ በአዕምሮአቸው ሚዘናዊ፣ በሰሜታቸው የማይበረግጉ ጽኑ አቂም የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች እንዲት ታሰሰቅ ሰዎች ሆኑ? ብቻ የመሆንን በረከት በአግባቡ ሰለ ተጠቀሙበት ነው። ብቻቸውን ሲሆኑ አእምሮአቸው አደዲስ የሆኑ ነገሮችን እንዲፈጥር አድሉን ተጠቀሙበት።

በዝመታ፣ በጸጥታ፣ በብቸኝነት ሕይወት የሚገኘውን ትልቅ ነገር ተገንዝበን ይሆን? ለብቻ መሆን በማይቻሰው ሕብረተሰብ፣ ጥድፊያና ሩጫ በሰዘበት ዓሰም፣ ራሰን ሰይቶ ለማወቅ፣ ብቻ መሆንን መማር ያሰፈልገናል። ብሩስ ቦርተን የተባለው ሰው፣ «ማንኛውም ሰው፣ እንዳንድ ጊዜ ራሱን ለብቻው ገሰል አድርጎ ማሰቀመጥ ቢማር፣ የዓሰምን ሕዘብ ይጠቅማል። ምክንያቱም በዓሰም ሰይ የተፈሰሰፉት ታሰሰቅ ነገሮች፣ ሰዎች ብቻቸውን በሆኑበት ጊዜ የተገኙ የፍልስፍና ውጤቶች ናቸው» አለ።

ብቸኝነት ብቻ ከመሆን የሚመጣ ሰይሆን፣ ውስጣዊ ስሜት ነው። ሰሕይወቱ መርከታን ያጣ፣ ሰሕይወቱ ትክክለኛ ዓሰማ የሌለው ሰው፣ ከሕብረተሰቡ ጋር አብሮ የመኖር ችግር ያጋጥመዋል።

ሰው ብቸኝነት እንዲሰማው ከሚያደርጉት ምክንያቶች ሌሰው፣ ሰው ራሱን ከልሎና ደብቆ ሲያስቀምጥ ነው። ይህን ዓይነቱ ሰው እውነት ከሆኑ ነገሮች ለመሸሽ ይሞክራል። «ምንም ነገር ከሰዶረግሁ፣ እጁን አጣምሬ ከተቀመጥኩ፣ ማንም የሚጎዳኝ ሰው አይኖርም» ይሰል። አጎዳሰሁ የሚል ፍርሃት ጪምድደ ሲይዘው፣ የመሥራት፣ የመሸሸል፣ እንዲሁም ሰሕብረተሰቡ ጠቃሚ ነገር ሰማከፈል አጁን ሰብሰበ ይቀመጣል።

አንዳንድ ሰው «ለመሞከር እፈራለሁ። ብሞከርም እንዳማይሰክልኝ አውቃለሁ። እወድቃለሁ፣ ሰወድቅም አወዳደቄ ታሳቅ ይሆናል» ይላል። ይህን ዓይነት ፍርሃት ያለበት ሰው እንደ አጋጣሚ ሆኖ ነገሮች ልከ በይመጡለት፣ መልስ ለማግኘት እንደገና አይሞከርም። በዚህ ምክንያት እርምጃው ጥንቃቄ የሞላበት ይሆናል።

«ጌታ ሆይ በብቸኝነት ስለቃይ ለምን ዝም ትለለህ?» የሚለው ሰው እግዚአብሔር ፊጽሞ የረሳውና የተወው ይመሰለዋል። እግዚአብሔር ላይ ከማማረር፣ ብቸኝነታችንን ልናጠፋበት የመንችልበቸው መንገደች ይኖሩ ይሆን? አንደኛው መንገድ፣ ሌሎች እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ስንረዳ ነው። እነርሱን ለመርዳት ስንታገል፣ እራሳችንን እንረሰለን። ብዙ ጊዜ ብዙ ብቸኛ የሆኑ ሰዎች እራሳቸውን በጣም የሚወዱ፣ በራሳቸው ላይ ብቻ ያተኮሩ ሰዎች ናቸው። የሚያስቡት፣ የሚጨነቁት፣ የሚታገሉት ለራሳቸው ብቻ ነው። ከራሳቸው ውጪ ሌላ ሀሳብ የላቸውም።

በለንበት ቤተ ክርስትያን፣ በለንበት ሕብረተሰብ፣ ሌሎችን ለመርዳት እንሞከር። ሌሎችን መርዳት እራሳችንን መርዳት ነው። የሌሎችን ሕይወት ወደ በጎ ለመለወጥ ስንታገል፣ የእኛም ሕይወት አብሮ ይለወጣል።

ሁለተኛ፣ ብቸኝነትን ለማጥፋት፣ ከለው ሁሉ ጋር በሚቻለን አቅም በፍቅርና በእውነት ለመኖር እንሞከር። «የሚቻላችሁ ቢሆን፣ ከለው ሁሉ ጋር በሰላም ኖሩ፤ በእናንተ በኩል የሚያስፈልገውን ሁሉ አድርጉ» (ሮሜ 12፣18)።

«ከእከሌና ከነእከሌ ጋር በፍጹም ልስማማ አልችልም» የሚለውን እበበል ጠርሶ እናስወግድ። ይሄ መንፈሳዊ ዓይናችንን ያሰውራል፤ መንፈሳዊ ሕይወታችን እንዲያድግ ጠምድደ ይይዘዋል። ከሰው ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ከማጥበቡም በላይ ጠርሶ ይገድለዋል።

ሦስተኛ ብቸኝነትን ለማጥፊት የሚረዳን «ለዎች እኔን አይወዱኝም» የሚለውን ሰሜት ማስወገድ ነው። «ሰሜትን» ከተጨበጠ እውነት መለየት እንቻል። «የሚጠሉኝ፣ የማይፈልጉኝ፣ የማይቀበሉኝ ይመስለኛልና» «ይጠሉኛል፣ አይፈልጉኝም፣ አይቀበሉኝም ከሚለው ይለያል። በዙሪያችን በብዙ ሰዎችና ወዳጆች ተከበን ብቻችንን የሆንን የሚመስለን ጊዜ አለ። ያ ሰሜት ነው እንጂ እውነት አይደለም።

ኢየሱስ «አብ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም» አለ (ዩሐ 16፣32)። ለብቸኝነት ትልቁ መድኃኒት እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ መኖሩን ማመንና መቀበል ነው። «ጌታ ከእኔ ጋር ነው፣ ብቻዩን አይለሁም» በማለት የብቸኝነትን ስሜታችንን እናስወግድ።

4

በሕመም ስንሰቃይ
እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?

በህመም ስሚሰቃዩና ተበፋ ሰቆረጡ ሰዎች ምን ዓይነት የማጽናኛ ቃል እንደምንበጣቸው ብዙ ጊዜ ግራ ይገበናል። ብዙ ጊዜ ብቸኞች ናቸው። በታለቅ መከራ ውስጥ ስለሉ የምንሰጣቸው ምክርም ሆነ የማጽናኛ ቃል፣ ጋይል የሌለውና ፍጹም ድርቅ ያለ ነው።

እማሪና ተዋበች ሁለቱም ጌታን የሚወዱ ጠንክራ ክርስትያኖች ናቸው። በዕድሜያቸው ገና ሃያ ውስጥ ናቸው። በመከላሳቸው ፍጹም የሆነ ፍቅር በለ ነበረ፣ የተቀረውን ዘመናቸውን አብረው ለማለለፍ የጋብቻን ሕይወት ጀመሩ። የጋብቻ ሕይወት ለእማሪና ለተዋበች ፍጹም ውብና ጣፋጭ ነበር።

በዚህ ዓይነት ሕይወት ብዙ ጊዜ አልቆዩም። ድንገት ተዋበች ታመመች። ጋኪም ቤት ሄዳ ስትመረመር ካንሠር እንደለበትና የመዳን ተሰፋዋም በጣም የመነመነ እንደሆነ አወቁ። በመከከላቸው ትልቅ ሀዘንና ድንጋጤ ወደቀባቸው። የሀዘን መጋረጃ ቤታቸውን ከደነው። ደበታቸው ተገፈፈ።

ተዋበች ሕመሙ እየበረታበት ሲሄድ ሆስፒታል ገብታ ሕክምና ጀመረች። ካንሠሩን ለማውጣት ከብብቷ እስከ ሆዷ ድረስ አፐራሲዮን ሆነች። ያም ሆኖ የመዳን ተበፋዋ ከመቶ ሃምሳ ብቻ ነበር። በዚህ ምክንያት ተዋበች ሥጋዋ ተዳክሞ የአልጋ ቁራኛ ሆነች።

እማሪም ኑሮ ጪለመበት፤ ተበፋ ቆረጠ። ተዋበች ሞታ በምን ዓይነት ጋይል ለብቻው ለመኖር እንደሚችል አለወቀም። የዕለት ሥራውን ማከናወን አቃተው። «እግዚአብሔር ሆይ! ለምን?--ለምን? ለምን ተወበች ትታመማለች? ለምን ተወቡ ትሞታለች» እያለ ቀንና ሌሊት ያለ ቅለል፤ ይጠይቃል።

ተዋበችና እማሪ ሁለቱም ጠንክራ ክርስትያኖች ቢሆኑም በጌታ ላይ የነበራቸውን ምሬት አልሸሸጉም። «እግዚአብሔር ሆይ፣ ለምን በእኛ ይህ ደረሰ? ጣፋጩን የጋብቻ ሕይወት ለአጭር ጊዜ ብቻ ለምን አቀመበከን?» በማለት ከእግዚአብሔር ጋር መጠያየቃቸውን አለቆሙም።

ተዋበች በሚሰጣት ሕክምና (ኬሞ ቴራፒ) ምክንያት ሰውነቷ እየወደቀ መጣ። ያ ቁንጅናዋ ሁሉ ጠፋ። ጸጉሯ ረገፈ። ቆዳዋ እንደ ጥለሸት ጠቆረ። ይደከማታል፤ ሁልጊዜ ጉሮሮዋ ይቆበለል። ጉሮሮዋ እየቆሰለ መዋጥ ስለልቻለች ሀኪሙ ሰጊዜው የሚሰጣት ሕክምና አንዲቆም አደረገ።

ተዋበች በተለይ ህክምና ሲደረግለት ሁልጊዜ በለ በቃይና በለ እግዚአብሔር ታሰበለች። ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትያኖች ይደግፈናል፣ ያጽናኑናል ብላ ገምታ ነበር። በኋላ ግን ንግግራቸውና ምክራቸው የበለጠ አደናጋሪ እንደሆነ ተገነዘበች።

የቤተ ክርስትያናቸው ዲያቆን ከነበሩት መካከል አንደኛው ተዋበችን ሊጠይቅ እንድ ቀን ሆስፒታል መጣ። ሁኔታዋን አይቶ ልቡ በጣም አዘነ። ያጽናናታል ብሎ የገመተውን ቃል መስንዘር ጀመረ። «ተዋበች! ይገባኛል ስቃይሽ ትልቅ ነው። እግዚአብሔር እንድ ነገር በሰው ሕይወት እንዲደረሰ ሲያደርግ ምክንያት አለው። ጌታ ሕይወትሽን ሲያይ አርሱን ደስ የማያሰኝ ኃጢአት በሕይወትሽ አይቶ ይሆናል። ምናልባት ከእርሱ ፈቃድ ውጪ ወጥተሽ ሊያስተካክልሽ ይሆናል። እነዚህ ነገሮች ሁሉ ያለ ምክንያት እንዲሁ አይሆኑም። እግዚአብሔር ምን ሊነግርሽ፣ ወይንም ምን ሊገልጽልሽ እንደሆነ አውቀሽል?» አሳት። ተዋበች በመጽናናት ፈንታ ይበልጥ ተረበሸች።

በሌላ ቀን ደግሞ የቤተ ክርስትያናቸው መጋቢ ሚስት ተወበችን ልትጠይቃት ሆስፒታል መጣች። ይህች ሴት በሰሜት የሰከረች፣ እንግዳ ትምህርት ሞልቶ የተረፈት ናት። ከዚህም ከዚያም ጥራዝ ነጠቅ ትምህርቶችን ለቃቅማለች። «በሽታ ከእግዚአብሔር አይለም፣ ሰይጣን በሕይወትሽ እየሠራ ነው። ለመፈወስ እምነት አስኪኖርሽ ድረስ እግዚአብሔር እየጠበቀሽ ነው። በቂ እምነት ቢኖሮሽ ትፈወሺ ነበር። አስታውሺ ተዋቡ! እምነት፣ እንቧን ከንሥርን ቀርቶ ተራራን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያንቀሳቅሳል። እግዚአብሔር ሊፈውሰሽ እንደሚችል በፍጹም ልብሽ ብታምኚ ጌታ ይፈውስሻል» አለቻት።

ተዋበች የተሰጣትን ምክር ሁሉ በጥንቃቄ እደመጠች። ሊያድናት የሚችል በቂ እምነት እንደሌት ተሰማት። ይሁን እንጂ እምነቷ ከልቧና ከእውነት መሆኑን እግዚአብሔርን እንዴት እድርጋ እንደምታሳምነው ግራ ገባት። እምነት ጡንቻ አይደለም። ጡንቻ በልምምድ እንደሚደብረው፣ እምነትን በዚያው መልክ ማደበር አይቻልም። ሙልጭልጭ ነገር ስለሆነ በሥራ ላይ ማዋል ያሰቸግራል። ተዋበች እምነቷን በሥራ ላይ ለማዋል ፍፁም ግራ ገባት።

በሌላ ጊዜ ሌላ ክርስትያን ወንድም ተዋበችን ለመጠየቅ መጥቶ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምክር ትቶላት ሄደ። «<u>በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን አመስግኑ</u>» የሚል መጽሐፍ ከዚህ በፊት እንብቧል።

በነበበው መጽሐፍ መሠረት ተዋበችን ለመምከር ተነሳ። «ተዋበች! ጌታ ሆይ ቤሕመም እንድሰቃይ ስለ እደረግሽኝ እመበግንሃለሁ፣ ይህ የእንተ ፈቃድ ነው። መልካም ነገር ለእኔ ምን እንደሆነ አንተ ታውቃለህ። ጌታ ወደሽኝ ይህን እንዳይና እንድለማመድ ስለ እደረግሽኝ እመሰግንሃለሁ። በሁሉም ነገር እመሰግንሃለሁ» በይው አሳት።

ተዋበች ይህን ምክር ከሰማች በኋላ እግዚአብሔርን በአዕምሮዋ መሰል ጀመረች። እግዚአብሔርን በሰማይ ላይ እንደ ተቀመጠ ግዙፍ ነገር እድርጋ እየችው። ይሽው ግዙፍ ኃይል በምድር ውርውር የሚሉትን ሰዎች ከመራት ብድግ አድርጎ ከአንድ ሹል ድንጋይ ጋር አጣብቆ «ጌታ ሆይ ይህን ነገር ስለኔ እንዲደርስ ስለ እደረግህ እመሰግንሃለሁ» ብለው አስኪሙሁ ድረስ እጥብቆ ይዘ እየችው። ይህን የመሰለውን እግዚአብሔር መውደድም ሆነ ማምለክ አልቻለችም።

በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰለና አስተዋይ የሆነ እንድ ክርስትያን ወንድም ተዋበችን እንዲህ ቢል አጽናናት። «ተዋበች! ክርስቶስ መከራን እንደቀመሰ እንቺም እርሱን እንድትመስይው መከራን እየቀመስሽ ነው። አብረሽው መከራ ስለ ተቀበልሽም ሽልማትሽን በሰማይ ይሰጥሻል። ኢዮብን እንደ መረጠው እንቺንም ለሌሎች ምሳሌ እንድትሆኚ፣ ኃይልሽንና ታማኝነትሽን ተመልክቶ በዚህ መከራ ውስጥ እንድታልፊ መረጠሽ። እንቺ በመከራሽ ታግሰሽ ሰታልፊ በማየት ሌሎች አይተው እንዲጽናኑና እምነታቸው እንዲጠነክር ለምሳሌነት ተጠቀመብሽ» አለት።

ተዋበች በተለይ ህመሙ ሲያበቃያት፣ ሲያስጨንቃት፣ የቀመሰችው ትንሽ ምግብ እንኳን በትውከት ቢወጣ፣ ፊቷ ገርጥቶና ያለ ዕድሜዋ አሮጊት መሰላ ራሷን ስታይ ወደ እግዚአብሔር እየጮኸች «ለምን በእኔ ላይ ይሄ ደረሰ? በሚሊዮን የሚቆጠሩ ከእኔ ሺ ጊዜ የሚበልጡ ጠንካራ ክርስትያኖች እያሉልህ ለምን እኔን ለዚህ ነገር መረጥከኝ» ትላለች። እኛስ ብንሆን ዘራ ተዋበችን ለመሰሉ፣ በበሽታ ለሚሰቃዩ፣ ከሳይ ከሰማነው ምክርና የማጽናኛ ቃል የተሻለ ምን መናገር እንችላለን? የሚሰቃየውን ሰው እንረዳው ይሆን ወይንስ የበለጠ ግራ እናጋባው ይሆን?

ከሰይ ታሪኳን ያነበብነው ተዋበች ስለ ህመሟ የተሰያየ አስተያየትና መግለጫ ሰማች።

--«በሕይወትሽ ኃጢአት ቢኖር ነው፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ወጥተሽ ይሆናል»

--«በቂ እምነት ቢኖርሽ ኖሮ ትፈወሺ ነበር»

--«በህመሜ እንድሰቃይ ስለ አደረገሽኝ አመበግንሃለሁ» በይው»

--«የመከራው ተከፋይ እንድትሆኚ መረጠሽ-- በእንቺ መጽናት ሰሌሎች መጽናኛ እንድትሆኚ ነው» የሚሉ አስተያየቶች ነበሩ።

በአሁኑ ጊዜ ብዙ አወናባጅ ትምህርቶችና ስብክቶች አሉ። በህመም የሚሰቃየውን ሰው ከሚያጽናኑት ይልቅ ይፈርዱበታል። «በኃጢአቱ ይሄ ደረሰበት» በማለት የፍርድ ቃላቸውን ያሰሙታል። ስለ ሆነም ከርስትያኖች በመከራ ውስጥ ሲያልፉ ወደ ከርስትያኖች ዘንድ ሄደው ከመጽናናት ይልቅ ከርስትያኖችን ይሸሻሉ።

ከርስትያን የሆነ ፍጹም ከሕመም ነፃ መሆን አለበት ብለው ያስተምራሉ። ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በበሽታ ይሰቃዩ ስለነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች በተሰያየ ሥፍራ ተጽፎ ያነበቡ አይመስለኝም። አንድ ጊዜ ጳውሎስ በጣም ታሞ የገሰትያ አገልግሎቱ ከባድ ሆኖበት ነበር። «በመጀመሪያ በሰበኩላችሁ ጊዜ በህመም ሳይ እንደ ነበርሁ ታውቃላችሁ። ምንም እንኳ ሕመሜ ፈተና ቢሆንባችሁም አልናቃችሁኝም ወይም አልተጸየፋችሁኝም» (ገላት 4፣13-14) ይላል። ኤልሰዕ በልታወቀ በሽታ ታሞ እንደ ሞተ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። (መ ነገሥት ካልዕ 13፣14)።

ጳውሎስ በመልዕክቱ ሦስት የተሰያዩ በዎች ሕመም እንደ ነበራቸው ይገልፃል። ጢሞትዮስ የሆድ ህመም እንደነበረበት (1ኛ ጢሞ 5፣23) ይናገራል። ስለ እፍሮዲጡን ሲጽፍ «በእውነት ታሞ ሰሞት እንኳ ቀርቦ ነበርና ነገር ግን እግዚአብሔር ማረው» ይላል (ፊሊ 2፣27)። ሌላው ደግሞ ጥርፊሞስ ነው። ጳውሎስ መታመሙን ሲገልጽ

«ጥሮፊሞስን ግን ታሞ በሚሊጠን ተውሁት» ይላል (2ኛ ጢሞ 4፣20)። ከሰይ ሰማቸውን የሰማናቸው ሁሉ ታስሰቅ የእግዚአብሔር ሰዎች ቢሆኑም በህመም ተስቃይተዋል።

ታመው የማይፈወሱ ሰዎች በሕይወታቸው ኃጢአት ቢኖርባቸው ወይንም እምነት ስለ ሌሳቸው ነው የሚሉ አስተማሪዎች እዮብን ሰማጽናናት የመጡትን ጊደኞቹን ይመስሰሉ። ኤልፋዝ፣ በልደደስና ሰፋር፣ ሰው የሚሰቃይበት ምክንያት ፃድቅ ስሰልሆነ ብቻ ነው ሲሉ እምነታቸውን አጸኑ። «ኢዮብ የሚሰቃየው የተደበቀ ኃጢአት ቢኖርበት ነው» ሲሉ ፈረደበት። መራራ የሆነውን የፍርድ ቃል ለብዙ ሰዓት አሰሙት። እነርሱ ይፍረዱበት እንጂ እግዚአብሔር ግን ፍጹም መሆኑን ተናግሮለታል (ኢዩብ 1፣8)።

በምክራቸው ሦስቱም መስመር የለቀቁ በመሆናቸው እግዚአብሔር ይቅር እንዲሰቸው ኢዮብ ሰሦስቱ ጊደኞቹ እንዲጸልይሰቸው ነገረው። ዛሬም የኢዮብ አጽናኞችን የሚመስሉ እንደንድ ሰዎች አሉ። ያዘኑና የተቆረቆሩ ይምስሉ እንጂ ከአፋቸው የሚወጣው የፍርድ ቃል ነው። እግዚአብሔር ያልሰጣቸውን ቃል «እግዚአብሔር እንዲህ ይሰል» ሲሉ በድፍረት ይናገራሉ። የታመመው ሰው በበሽታ ከሚሰቃየው ይበልጥ የእንዳንድ ከርስትያኖች የፍርድ ቃል ያስቃየዋል። ሕመሙን ከሚፈራው ይልቅ ከርስትያኖችን ይፈራል።

እኔና ቤተሰቤ በእግዚአብሔር እጅ የምንታሸበት ዘመን ነበር። የተሰየያዩ ችግሮችና ፈተናዎች ይፈራረቁብን ነበር። ሁኔታዎቹ ከባድ ቢሆኑም፣ በእግዚአብሔር ጸጋና ድጋፍ በትዕግሥት በውሰጡ ማሰፍ ቻልን።

ቀደም ሲል ያሰፍንበት አልበቃ ብሎ ሌሳ ችግር አጋጠመን። ሁሰተኛው ልጃችን፣ ገና የአንድ ዓመት ልጅ ሆኖ፣ ያለ እንዳች ምክንያት ከፊቱ ሳይ አጢ የሚመስል እብጠት ወጣበት። ቶሎ ወደ ሆስፒታል ይዘነው ሄድን። ሀኪሙ መረመረውና «መተኛት አሰበት» አሰን። ደነገጥን፤ ድንጋጤአችን ከባድ በሽታ ነው ብለን እይደለም። የደነገጥነው «ሆስፒታል ይተኛ» ስለአሰን ነው። «ታዲያ ሆስፒታል ገብቶ መታከሙ

ምን ያበደ ነግጣችሂል?» ያሰኛል። የደነገጥነው እሁንም ገንዘቡን ፈርተን አልነበረም።

የፈራነው ከርስትያኖችን ነበር። «በኃጢአታቸው ምከንያት ይሄ ደረሰባቸው» ይሉናል ብለን ሰጋን። ልጃችንን ሆስፒታል ሰናስገባ በተመሰሰሸ አንዲታከም ሀኪሙን አጥብቀን ለመንነው ። ሀኪሙ ግን «አይሆንም» አለ። በመጪ ረሽ በማግሥቱ ልጃችንን ይዘን ሰምጣት ተስማምተን ወደ ቤታችን ሄድን።

እቤታችን ገብተን እኔና ባለቤቴ መወያየት ጀመርን። ሰው ሳያውቅ በድብቅ እናስገባው፤ ሰማንም እንናገር። ሴሰው ቀርቶ ለቤተሰባችን እንኳን ሳለመናገር ተስማማን። በማግሥቱ ልጃችንን ሆስፒታል አስገባነው። ሆስፒታሉ ውስዮ ከርስትያን ነርሶች ስለ ነበሩ ጉዳዩ ምስጢር ሳይሆን ቀረ። የእኛን በጎነት የማይፈልጉ እንደንድ ከርስትያኖችም የልጃችንን ሆስፒታል መግባት ሰሙ።

እንደፈራነውም አልቀረልንም። «አይዘእችሁ፤ በርቱ ብሎ ያጽናናን ሰው አላገኘንም። በዚያ ፈንታ ግን ልባችንን የሚሰብር ከእንዱ ደብዳቤ ተፃፈልን። ማንነቱ እንደይታወቅ ስሙን አልፃፈም። በትልቁ እንደ አርዕስት የተጠቀመው «እይ የሸማግሌያችን መከራ!» የሚል ነበር። በደብዳቤው ሳይ የተገለጸው፤ መከራችን የበዛው ኃጢአተኞች በለሆንና ገና ወደ ፊት ከዚህ የበለጠ እንደሚደርበብን በመግለጽ ነው።

ሰጊዜው ደብዳቤው ልባችንን ሰበረው። እበከ ዘራ ድረስ ያን ደብዳቤ ማን እንደጻፈልን አናውቅም። ይሁን እንጂ ለእኛ ትልቅ ትምህርት ትቶልን ሄደል። በውስጡ በሰለፍን ከዚያን ጊዜ ወዲህ የሴሎች ቁሰል፤ የሴሎች በወንድሞች መወጋት ይሰማናል። በመከራ ውስጥ የሚያልፈውን ሰው እንድናጽናናው፤ ደግፈን እንድንይዘው ልዩ ሸከም ይሰማናል። ድንጋይ ከሚወረውሩት ጋር በመተባበር ድንጋይ ሳስመወርወር፤ ከወርዋሪዎች ወገን ከመሆን፤ ከሚወረወርባቸው ወገን መሆንን መረጥን።

«እግዚአብሔር በሕመም ስበቃይ እያየ ሰምን ዝም አለ?» ብለን

መጠየቃችን አይቀርም። ፈራጆች እንደ ሚፈርዱት «በኃጢአቴ ምከንያት መጣብኝ» የሚሰውን የተሰበተ አባባል ከአዕምሮአችን እናስወጣ። ሰው በኃጢአት ምከንያት በሽታ የሚመጣበት ቢሆን ኖሮ በዚህ ዓሰም ሳይ ጤናማ ሕይወት መኖር የሚችል ሰው ባልኖረም ነበር። ምከንያቱም ሁሳችንም ኃጢአተኞች በመሆናችን ነው።

--<u>በፈውስ አምናለሁ</u>። እግዚአብሔር እንድንፈወስ ይፈልጋል። ከበሽታችን ለመፈወስ እግዚአብሔርን በዕምነት እንጠይቀው፤ በተበፈም እንጠብቀው።

--<u>በሕክምና አምናለሁ</u>። «እምነት ያለው ጥሩ ከርስትያን ሀኪም ቤት መሄድ የለበትም፣ መድኃኒት መውሰድ የለበትም» የሚሉትን አስተማሪዎች፤ ትምህርታቸው ገለበ የበዛበት በለ ሆነ አልቀበልም። እንዳንድ የዋህ ሰዎች የእነዚህን «ገለበ ትምህርት» የተከታተሉ፤ ልጆቻቸው ሲታመሙ ሀኪም ቤት አልወስድም በማለት በሞት አጥተዋቸዋል። ሕክምና እግዚአብሔር ከዘጋጀልን መልከም ነገር እንዱ በለ ሆነ፤ ከመጠቀም ወደ ኋላ እንበል። ሀኪም በመጠቀማችን «እግዚአብሔር መፈወስ አቅቶታል» ማለታችን አይደለም። ለሀኪሞች ጥበብን የሰጠ እርሱ እንደሆነ እናምናለን።

የባለቤቴ እናት ዘጠኝ ሰዓት የፈጀ የእንጎል ቀደ ጥገና ተደርጎላቸዋል። በሰው ዓይን ሲገመት በሕይወት የመኖር ዕድላቸው በጣም ትንሽ ነበር። ይሽውና ሕክምናው ከተደረገላቸው አሥራ ሁለት ዓመት ሆነ። ጤናማ ሰው ሆነው ቀንና ማታ በጌታ ፊት እየተነበረከኩ ያመሰግኑታል። ጌታ ተጪማሪ ዕድሜ ሰጥቶአቸው ደስ ብሎአቸው ይኖራሉ።

በፈውስ የምናምን ከርስትያኖች በለ ነበርን ሀኪም ቤት ከመውሰዳችን በፊት በዙ ጊዜ እየጸምን ጸልየናል። ጌታ ያኔ ሊፈውሰቸው ይችል ነበር። እርሱ መሥራት እቅቶት ከሰው እርዳታ እንደማይፈልግ እናውቃለን። ይሁን እንጂ ፈውሰቸው እኛ በፈለግነውና በጠበቅነው መንገድ አልሆነም። እግዚአብሔርን «በዚህ መንገድ ብቻ እንድትፈውሰቸው ነው የምንፈልግው» በማለት ልናዘው እንችልም።

እርሱ በመረጠው መንገድ ሊፈውሰቸው ይችላል። «ሀኪም ቤት አንወበዳቸውም፣ በጸሎት ብቻ መፈወበ አለባቸው» ብለን ብንተዋቸው፣ በአንጎላቸው ውበጥ የነበረው ዕጢ አድጎ ከውስጥ ፈንድቶ ይሞቱ ነበር። በሀክምና ስለዳኑ እግዚአብሔር አለዳናቸውም ብለን አናምንም።

እግዚአብሔር ወዲያው ሊፈውሰቸው ሲችል ሌላ መንገድ የመረጠበት ምክንያት ነበረው። እርሰቸውም የእግዚአብሔርን ድንቅ አሠራር ማየት ቻሉ። ልጆቻቸውም ከምንጊዜውም ይበልጥ የጌታን ክንድ ማየት ቻሉ። ስለዚህ ሀኪም ቤት መሄድ ኃጢአት ነው የሚለውን አበተሰበብ አስወግዳችሁ በሕክምና ተጠቀሙ።

<u>በእምነት እንዳንፈወስ እንቅፋት የሚሆነውን ሁሉ</u> እናበወግድ። እምነታችንን የሚያዳክመውን ማንኛውንም ነገር ክሕይወታችን እናበወግድ። በእኛ በኩል ለፈውሰችን እንቅፋት ይሆናል ብለን የምናበበውን ሁሉ ሕይወታችንን እየመረመርን አውጥተን እንጣል። ሕሊናችንን የሚቆረቁረን ኃጢአት ቢኖር ሰይጣን እንዳይከሰን በንበሀ ለጌታ እናቅርበው። በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ላይ ጥሰቻና መራራ ሕይወት ከሰን ይቅር እንበሰቸው።

ይህን ሁሉ አድርገን ከልተፈወበን፣ «እግዚአብሔር የፈለገውን በሕይወታችን ይሥራ» በማለት እርሱን በመተማመን ዕለታዊ ኑሮአችንን መኖርን እንቀጥል። በሕይወታችን እኛ ያለየነውን ነገር ጌታ ክገለጸልን፣ እንደ ገና ለፈውበ መጸለይ ጪርሰ እናመንታ። አሁንም ቢንፈወስ፣ የበደለኛነት ስሜት እንዲሰማን አያስፈልግም። ሙሉ በሙሉ በእርሱ በመተማመን ኑሮአችንን እንቀጥል። በሥጋዊ ፈውስ ላይ ብቻ ከማተከር፣ ነፍሰችን፣ በሜታችን፣ ጋብቻችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረን ኅብረትና እንድነት እንዲፈወበ አጥብቀን እንጸልይ።

«በበሽታ ስሰቃይ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?» የሚለው ጥያቄያችን ገና መልበ አላገኘም።

እግዚአብሔር በዓለም ላይ መከራን፣ በቃይንና በሽታን በመፍቀዱ የሚከሱት ሰዎች አሉ። በተለይ በውስጡ የሚያልፍ፣ ጭንቀት

ሲበዛበት እግዚአብሔርን መርገም ይጀምራል። የሁኔታው አሰሰቢነት በሩቅ ከሆነ አይሰማንም። ግን እኛን እራሳችንን ወይንም በቅረብ የምንወዳቸውን ሰዎች ሲመታ፣ ያኔ ይበልጥ ይሰማናል። ለምን በበሽታ በንሰቃይ እግዚአብሔር ዝም እንደሚል በእዕምሮአችን መልበ የማናገኝለት ጥያቄ ብቻ ሆኖ ይቀራል።

አንድ ነገር እርግጠኞች ነን። ክርስቶስ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ ከዚህ ዓለም በሽታና ሥቃይ ይኖራል። ይህም በሽታ የሚነክው የማያምኑትን ብቻ ሳይሆን አማኞችንም ያበቃያል።

ሌላ እርግጠኞች የሆንበት ነገር አለ። እግዚአብሔር ጠክኝ፣ በለዎች መከራና በቃይ ደስታ የሚሰማው አለመሆኑን ነው። የሁሰችንም ሕመምና በቃይ ይለማዋል፤ ያገባዋል። በህመም መሰቃየትን እያየን «ይሄ ለምን ይሆናል?» ብለን በቁጣና በንዴት በንጠይቅ፣ በሌላ ወገን ደግሞ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ጸጋውን እናያለን።

በተለይ በሕመም ስቃይ ውበጥ የሚያልፍ፣ የእግዚአብሔርን ሕያው የሆነውን ፍቅር በሕይወቱ የተቀበለ አማኝ፣ በጭንቀቱ መካከል እንኳን የእግዚአብሔርን ፍቅሩን፣ ደግነቱና ቸርነቱ እየታየው እውነተኛ ደስታና ሰላም በውስጡ ይፈሰል። ምንም ዓይነት የበሽታ ኃይል ቢሆን በውበጡ የተተከለውን የጌታን ፍቅር ከውስጡ ፍቆ እያወጣውም።

«የት ሄዷል እግዚአብሔር እኔ በበሽታ በቃይ ዝም የሚለው?»

<u>የትም አልሄደም</u>። እዚያው አጠገባችን ነው ያለው። በክፈው ዓለም ውበጥ በሚደርስብን መከራና ጭንቀት ምክንያት ዝለን እንዳንወድቅ፣ እምነታችን እንዳይጠፋ፣ በሰማያዊ ኃይሉ እያበታጠቀን ነው ያለው።

--<u>የትም አልሄደም</u>። የሚመረጥ መንገድ ባይሆንም፣ በዚያ ውበጥ ከዚህ በፊት ያልተማርነውን ዓይነት ልዩ ልዩ ትምህርት እያበተማረን ነው። የሰዎችን ወረተኛነት፣ በንሰቃይ እንዴት ቶሎ ጥለው እንደሚጠፉ፣ እግዚአብሔር ግን ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ

እያበተማረን ነው። «የሚያስተምርበት ሌላ መንገድ የለውም እንዴ?» ብለን መጠየቃችን አይቀርም። አለው፤ ግን የመረጠው ይህንን ይሆናልና በትዕግሥት የሚያስተምረንን እንማር።

<u>የትም አልሄደም</u>። በበሽታ ስንሰቃይ «ለምን እግዚአብሔር ይህን አደረሰብኝ» በማለት የበድብ ቃል እናበማ እንደ ሆነ ይጠብቀናል።

<u>የትም አልሄደም</u>። በመከራችን ውስጥ መንፈስችንን ለማደስ በመለኮታዊ ኃይል እያስታጠቀን ነው። ሥጋችን በህመም ቢሰቃይና ቢደከምም፣ ነፍስችን የታደሰች ነች።

<u>የትም አልሄደም</u>። በሰቃያችን ጊዜ ከእኛ ጋር ነው። አብሮን እየደማ፣ አብሮን እየተሰቃየና እያለቀሰ ነው። በመከራቸው ውስጥ አብሮአቸው በመሆን ስቃያቸውን በበማያዊ ሥፍራ ከፍተኛ ቦታ እንዲያገኝ እያከበራቸውና እያስከበራቸው ነው።

<u>የትም አልሄደም</u>። በአሁኑ ጊዜ ከእኛ ጋር ነው። በመንፈስ ቅዱስ የማጽናኛ ቃሉን እየሰጠ እያጽናናን ነው።

<u>የትም አልሄደም</u>። ሠራዊቱን እየሰበሰበ ነው። አንድ ቀን ከነሠራዊቱ ይመጣል። ያኔ ለመጪረሻ ጊዜ ሕመምንና ስቃይን ያጠፋል። አዲስ ዓለምን ይበጠናል። በዚያም ሕመምና ስቃይ አይኖርም።

5

በእጦት ስንሰቃይ እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል?

አደፍርስ በጥንቃቄ ሕይወቱን የሚመራ ብርቱ ከርስትያን ነው። የራሱን የከርስትና ሕይወት ጠብቆ የሚኖር በቻ ሳይሆን፣ በልዩ ልዩ አገልግሎቶች በመግበት ጌታን የሚያገለግል ወንድም ነው።

አደፍርስ የሰባት ልጆች አባት ሲሆን፣ መጠነኛ ሥራና መጠነኛ ገቢ ያለው ነው። የኑሮ ጥበት በጣም አለበት። ለራሱና ለቤተሰቡ የሚፈልገውን ማድረግ የሚያስችል የገንዘብ ኃይል የለውም። በወር ገቢው ለወር አበከ ወር ለመድረስ ብዙ ይቸገረዋል። አንዳንዴ ሳይታሰብ ልጆቹ ይታመሙበትና ሆስፒታል ይዘ ይሄዳል። መድኃኒት መግዣ በማጣት በጣም ይቸገራል። በዕድሜ ገና ሕፃን የሆነ ልጅ በሳለው አልፎ አልፎ ወተት መግዣም የማይኖራቸው ጊዜ አለ።

እደፍርስ ለልጆቹ አዲስ ልብስ ለመግዛት በለመቻሉ የልጆቹ ልበስ ብዙ ጊዜ የተለጣጠፈ ልብስ ነው የሚያለብሳቸው። ሚስቱማ አዲስ ቀሚስ ከየች ብዙ ጊዜ ሆኗታል። እንደ እንዳንድ ሴቶች «ቀሚስ ግዛልኝ» ብሰ የምታስጪንቀው ብትሆን ምን ይውጠው ነበር?

እደፍርስ ከጌታ ጋር በቅርብ የሚኗዝ ቢሆንም፣ በኑሮ ጥበት፣ በማጣት፣ ምክንያት ምርር እያለው «በእሞት ስለቃይ እግዚአብሔር ሆይ! ሰምን ዝም ትለለህ?» በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ሙግት የሚገጥምበት ጊዜ ብዙ ነው። ጮኸቱ ሰሚ ያጣ ስለ ሚመስለው ብዙ ጊዜ ተስፋ ይቆርጣል። ምን ማድረግ እንደለበትም ግራ ይገባዋል። «እግዚአብሔር በ ኑሮዬ የማይሰርከኝ ስለ ማይወደኝ፣ ጥሩ ከርስትያን ስሰልሆንኩ ነው» በማለት ያስባል።

ጌታ መሰይ ደግሞ ሌሰ ከርስትያን ወንድም ነው። ጌታን በጣም የሚወድ ብርቱ ከርስትያን ነው። ከሰው ሁሉ ጋር የመግበበት ችሎታ ያለው ጮሌ ነው። የሚፈልገውን ለማግኘት ከሚፈልገው ሰው ጋር ተቀራርቦ ወዳጅ ለመሆን፣ ይጠቅመኛል ብሎ የሚያስበውን ሰው ከመዳፉ እጅ ሰማስገበት ጊዜ አይፈጅበትም።

ጌታ መሰይ በሥጋዊ ኑሮው የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራል። «ጌታ ይመስገን፣ ጌታዬ የተትረፈረፈ ኑሮ ያኖረኛል። እርሱን ከወቅሁበት ቀን ጀምሮ ያጎደለብኝ ነገር ምንም የለም። በሥጋህም በነፍስህም እበለጽግሃለሁ፣ በማለት የገበልኝን ቃል እስከ አሁን አስጠፈብኝም። እንኳን እኔ፣ ውሽቼም ተርፎአቸው የድራሉ። ልጄቼ በአለበሰቸው ከለው ልጆች በሰይ ናቸው፣ ሚለቴ ከወንደች ሚስቶች ሁሉ በአለበሰሷ ትበልጣለች። በቤታችን የጎደሰ ነገር ምንም የለም። ከሰው እንበልጣለን እንጂ ከለው አንሰን እናውቅም። ጥሩ ሥራ አለኝ። በሥራዬ የተከበርኩ ነኝ። ከሥራዬ እበረራለሁ ብዬ አልፈራም። እሪ ስንቱን ቆጥሬው እችሰለሁ? በጠቅሰሰ ጌታ ይመስገን እንጂ ሌሰ ምን አሰሰሁ?» እያለ መንፈሰዊ ቋንቋ በመጠቀም ትልቀነቱን በደረለበት ሁሉ ማውራት ልማድ አድርጎ ይዘታል።

እደፍርስና ጌታ መሰይ የሚያመልኩት ከእንድ ቤተ ከርስትያን ውስጥ ስለሆነ በየሰምንቱ ይገናኛሉ። ጌታ መሰይ በየጊዜው «ምለከርነት አለኝ» እያሰ ከመድረኩ ሰይ ቆሞ «ጌታ ይህን እደረገልኝ፤ ያን እደረገልኝ» በማለት ሲመለከር ይሰማዋል። እደፍርስ በእዕምሮው እንዳንድ ጥያቄዎች ሰይፈጠሩበት አልቀሩም። እርሱ ምንም ያህል ጌታን ቢወድም በ ኑሮው ግን ጎስቋሳ፣ አራቱን ጠግቦ የማያድር፣ የልጆቹና የሚስቱ ልብስ አሰፋሪ፣ አስተማማኝ ሥራ የሌለው፣ በየወሩ የቤት ኪራይ መከፈል አቅቶት የሚቸገር መሆ ኑን ያውቃል።

የጌታ መሰይን ምስክርነት በመስማት ብቻ ሰይሆን፣ የተንዘዘና የተትረፈረፈውን ሕይወት ያያል። እርሱና ሚስቱ መኪና ሲለዋውጡ፣ «እነ እከሌ ሰፊቸውን ቀይረዋልና እኛም እንቀይር» በማለት ሰፊቸውን ሲለዋውጡ ያያል።

እደፍርስ ግራ ግብት ይለዋል። የእግዚአብሔርን ፍቅርና በህሪ ትከከለኛውን *መመመ*ልከት ያቅተዋል። «ለምን እኔ እንዲህ በእሞት ስለቃይ ሌሰው ግን፣ እንኳን እርሱ ውሽው ተርፎት ይኖራል?» በማለት አራሱን ይጠይቃል። «ጥሩ ከርስትያን ስሰልሆንሁ ይሆናል» በማለት ራሱን ለመመርመር ይሞክራል።

የእደፍርስና የጌታ መሰይ ታሪክ ፈጠራ ታሪክ ይሁን እንጂ፣ በብዙዎች አማኞች መካከል ያለና የሚታይ ነው። መኖሩ እያስደንቀንም፣ የምንለማው ምክንያት ግን ያስደንቀናል።

በዚህ አጋጣሚ እንዳንድ እንግዳ ትምህርት በመከተሰችን ብቅ ብቅ እያለ ለስሆነ፣ በጊዜው ትምህርት ሲሰጥበት ይገበል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በህብት ያበለጸጋቸው፣ እትረፍርፎ የሰጣቸው የእግዚአብሔር ሰዎች እንደነበሩ እናነበለን። ኢዮብ፣ አብርሃም፣ ሰለሞን፣ ዳዊት እንዲሁም ሌሎች በዙዎች ይገኙበታል። በግልጽ እግዚአብሔር በህብት እንደበለጸጋቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

ሌሎች ደግሞ እርምጃቸው ከእግዚአብሔር ጋር ቢሆንም፣ ህብት ያልነበራቸው፣ ድሃዎች የነበሩ ለዎች እንደ ነበሩ እናነበለን።

--የታወቀው ነብዩ ኤልያስ በረሀብ የመበለት እንጀራና ውሃ ሲለምን ይታያል።

-- ሙሴ ከንጉሥ ቤት ወጥቶ በበረሃ በግ ጠባቂ ሆኖ እናየዋለን።

-- ጳውሎስ ለ ኑሮው ድንኳን ሲሰፋ ተመልክተናል

-- ሃዋርያት እሣ እያጠመዱ፣ በእገልግሎት በተሠማሩበት ሥፍራ የተሰጣቸውን እንጀራ እየበሉ እገልግሎታቸውን ከደር እስከ ደር አሰፋፉ።

-- እራሱ ጌታ ኢየሱስ የድሃ መጠረሻ ነበር፣ ይኸውም

-- የተወለደው ብግርግም፣
--- የተኟዘው በተውሰት ጀልባ፣
-- ፉሲካ የሚበሳበት ቤት ያልነበረው፣
-- በተውሰት መቃብር የተቀበረ ነው።

እነ ጳውሎስ ድሃዎች የነበሩት እግዚአብሔር ሰላልወደዳቸው፣ እርምጃቸው ትክክል ባለመሆኑ እንደልደሆነ መረዳት ይህን ያህል አያሰቸግረንም።

የእግዚአብሔርን ቃል ያለአግባብ ገንጥለው በመውሰድ ልዩ ትርጉም እንዲኖረው የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። ብዙ ጊዜ ለራሳቸው እንዲመቻቸው አድርገው ይተረጉሙታል። እንደኛው "Name it and Claim it" (የምትፈልገውን ተናገር፣ የእኔ ነው ብለህ ያዝ) የሚል ትምህርትና የእምነት ፍልስፍና ነው። የሚጠቁመውበት ዋናው ጥቅሳቸው «ጠይቅ ይሰጥሃል» (ሉቃ 11፣9) የሚለው ነው።

ይህን ትምህርት እምና የተቀበለች እንዲት ከሪዳ፣ ደሰ የሚሰትንና ለብዙ ጊዜ ትመኘው የነበረውን ከርስትያን በሩቅ አይታ። «በጌታ በኢየሱስ ሰም፣ እንተ ወጣት ባሌ እንድትሆን በእምነት አጠይቃለሁ፤ እምኄ ተቀብያለሁና ባሌ ነህ፤ ምንም ማድረግ አትችልም» አሰች ይባሳል። «በጳሎት ማናቸውንም ነገር ብትለምኑ እንደሚፈጸምሳችሁ እመኑ የምትለምኑትም ሁሉ ይሰጣችሃል» (ማር 11፣24) የሚለው ቃል መገልገያ ጥቅሳቸው ነው።

እንዳንድ ሰዎች የሚያወፍር ጣፋጭ ምግብ እያዩ «በጌታ በኢየሱስ ሰም፣ ከዚህ ምግብ የቻልኩትን ያህል በእምነት እበላለሁ፣ ምንም ያህል ብበላም አያወፍረኝም» በማስት ይበሳሉ። ከጊዜ በኋላ ከብደት ጠምረውና ወፍረው እራሳቸውን ሲያገኙት፣ ማር 11፣24 «እንደ እነገሌ ሰምን አልሰራልኝም?» ብለው ይጠይቃሉ ይባሳል። ይህ ለብዙዎቻችን ሞኝነት ቢመሰልም በዚህ ትምህርት ለተያዙት ግን የእምነት እርምጃ ይመስሳቸዋል።

"Name it and Claim it"(ተናገር፣ ጠይቅ፣ የእኔ ነው ብለህ ተቀበል) በሚለው ትምህርት በጣም የሚያምን እኔ ከምኖርበት ከተማ የአንድ ቤተ ክርስትያን ፖስተር ሆኖ ያገለግላል። «ከዲሳክ መኪና በጌታ በኢየሱስ ሰም እፈልጋለሁ» ብሎ ተናገረ። ይህን ብሎ ጠዋት ወደ ቤተ ክርስትያን ለማገልገል ሄደ። ስብከቱን ከጨረሰ በኋላ «ከዚህ መከከል ጌታ ለባሪያዩ ከዲሳክ መኪና ሰጥ ይልሃል» ሲል ትንቢት ተናገረ። ከዲሳክ መኪና የነበረው ሰው ጌታን ከልታዘዝኩ መቅሰፉት ይደርሰብኛል ብሎ በመፍራት ከስብሰባው በኋላ የመኪናውን ቁልፍ ሰፖስተሩ አሰረከበ። ያንን መኪናውን እየነዳ የማር 11፣24 እንደሚሠራ ምስክርነቱን ማሰፋፋት ጀመረ።

እግዚአብሔር የጠየቅነውን አይሰጠንም ማለት አይደለም። እንደሚሰጠን አምናለሁ። ብዙ ጊዜ ለጥቶናል፣ ጠይቄው ያልሰጠኝም ጊዜ ብዙ ነው። ችግሩ እግዚአብሔርን «በሰጠኝ» ብቻ የምናውቀው ከሆነ ነው።

አንድ ጊዜ ከርስትያኖች ምስክርነታቸውን ሲሰጡ በጥሞና የሚያደምጥ ከርስትያን ነበር። ሁሉንም እደምጦ ከጨረሰ በኋላ፣ በጣም ተገረመ። ዘጠና አምሰት ከመቶ ምስክርነቱ «እግዚአብሔር ይህን ሰለ ሰጠኝ አመሰግነዋለሁ» የሚል ነበር። ስለሰጠ መመሰገን ይገባዋል እርግጥ ነው። ግን ባይለጥስ? ከሰጦታው ውጪ እግዚአብሔርን ሰማየት አንችልም ወይ? ሰለ እርሱነቱ ብቻ ሲመሰገን አይገባውም ወይ? በፈሰገው ምክንያት መስጠቱን ቢያቆምስ አይመሰገንም?

ሕዝቡ ኢየሱስን ሲያነግሱት የፈለጉበት ዋናው ምክንያት ሳይሠሩ ተቀምጠው ስመብላት ስለ ፈለጉ ነበር። በተአምር 5 ሺ ሰው ሲመግቡ አይተዋል። ሁል ጊዜ እንደዚህ እንዲሆንላቸው ይፈልጋሉና «እናንግሥህ» አሉት።

ዛሬም ክርስትያኖች በሕይወታችን ልናነግሰው የምንፈልገው ጊዜያዊ ነገር ስለ ሚስጠን ይሆን? ወይንስ ከዚህ ከጊዜያዊ ነገር በእሸገር ማየት እንችላለን።

አንድ አንድ ጮሌ ክርስተያኖች አሉ። በእሰት ተግባራቸው በመትጋትና ኑሮአቸውን ስቀጥተኛ መንገድ ስማሸሸል በመሞከር ፈንታ አቋራጭ መንገድ ይፈልጋሉ። በምንስጠው አገልግሎት ምክንያት በጣም ብዙ ደብዳቤዎች ከየሥፍራው ይደርሰናል። ስሚደርሰን ደብዳቤ መሠረት ምን ያህል ሰው ለእግዚአብሔር ቃል ጥማት እንዳስበት መገንዘብ ችያለሁ። አልፎ አልፎ ግን እኔ ልመልሰው የማልችለው ጥያቄ ይቀርብልኛል።

በቅርቡ በመደጋገም ደብዳቤ ጻፈልን። ስጠየቀው ጥያቄ እስፈለጊውን ሚሚለት ስለማንችል መንፈሳዊ ጽሁፎችን ብቻ ላክንለት። ያም ያረዘው አልመሰለኝም። ስሦስተኛ ጊዜ የጻፈልን ደብዳቤ ይህን ይመስላል «---- ለምን ችላ ብለችሁ ልመናዬን እንደናቃችሁት በእውነት እንቆቅልሽ ሆነብኝ። -- ዓይኔን ከሰው ላይ አንሰቼ ከጌታ መጠበቅን እያስተማረኝና ይህንንም ጥበብ እየገለጸልኝ ነው። ቢሆንም በእንዴ በክርስትስ አክል ላይ የተስያየን ብልቶች ስለሆንን፤ መተሳሰብና የእንዴን ሸክም ሌላው እንዲሸክም ክርስቶስ ምሳሌአችን ስለ አሳሰበን ነው። የክርስቶስን ልብ ይሰጠን ዘንድ ጸሎቴ ነው።»

«---ሰለ ብዙ ንዝነዛ ጎረቤቱን እየሰመነ እንደሰጪ ነቀው ተነስቶም የሚፈልገውን ሁሉ እንደሰጠው ሰው፤ ዛሬም እባክችሁ ተሰመኑኝ እያልኩኝ ጌታንና እናንተን ደጅ እጠናስሁ። --- በምትልኩልኝ ስማንኛውም መንፈሳዊ ገጽ ውስጥ $300 U.S. እድርጋችሁ ለኩልኝ፤ እደራ! ጌታ በሙላት ይባርዛችሁ» የሚል ነው። የዚህ ሰው

ጥያቄ $10 ወይንም $20 አይደለም። ሦስት መቶ ደላር ነው። እሚረከ ስመኖራችን ይህን ያህል ገንዘብ በቀላሉ የምናገኝ መስሎት ይሆናል። ያም ሆነ ይህ፤ ከርስትያን ብርቱ ሠራተኛ ሆኖ መታገል እንጂ አቋራጭ መንገድ አይፈልግም።

ከላይ ያነበብነው ደብዳቤ፤ በእንድ ሰኩል «ዓይኔን ከሰው ላይ አንስቼ ከጌታ መጠበቅን አስተማረኝ» ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ «እባክችሁን ስጡኝ» ብሎ ይጠይቃል። ሁለቱ አብረው አይሄዱም። ይህን ዓይነቱን ወይንም ሌላ ተመሳሳይ ዘዴ ስመጠቀም ሲያገኙ «ጌታ ባረከኝ» የሚሉ እንዳንድ ክርስትያኖች አሉ። ይህን ምስክርነት የሚሰሙ፤ ስ ኑሮአቸው የገንዘብ ጥሰት ደርሰባቸው የሚታገሉ፤ «እንዴ! ይሄ እግዚአብሔር ለምን እኔን አይባርከኝም? ለምን ያዳላል? በገንዘብ እጦት ስስቃይ ለምን ዝም ይላል?» በማለት በእግዚአብሔር ላይ ድምፃቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ያደርጋል።

ትክክል ባልሆነ መንገድ እግዚአብሔርን ብናከብር በዚያ ደስ የሚለው አይመስለኝም። መሰመር በስቀቀ ሁኔታ እግኙተን ከምናመሰግነው ይልቅ፤ አጥተን እፈትንን ለምስጋና አለመከፈታችንን ይመርጣል።

«የብልጽግና ወንጌል» (Prosperity Gospel) የሚስብኩ ሰባኪዮች የሚጠቀሙበት ዋና ጥቅስ 3ኛ ዩሐንስ ቁ 2ን ነው። «ወዳጄ ሆይ! በነፍስህ ደህና እንደሆንህ አውቃለሁ፤ እንዲሁም ኑርህ ሁሉ እንዲሰክልህና ጤንነትም እንዲኖርህ እጸልይልሃለሁ» የሚለው ጥቅስ ነው። ይህንን ጥቅስ በመጠቀም ማንኛውም ክርስትያን «ጤነኛና የበለጸገ መሆን አለበት» ሲሉ ያስተምራሉ።

ይህ ለለምታ ሐዋርያው ዮሐንስ ለጋዮስ በግል እንዲሆንለት የተመኘው የምኞቱ መግለጫ እንጂ ለክርስትያኖች ሁሉ የተስጠ የክርስትና ሕይወት መለኪያ አይደለም። «ጥሩ ክርስትያን ከሆነ ጤናማና በኑሮ የበለጸገ ይሆናል» ብለው ያስተምራሉ። የእግዚአብሔር ቃል ግን አማኝ ሁሉ «ጤነኛና የበለጸገ ይሆናል» የሚል ማረጋገጫ አልሰጠውም። ክርስትያን ድሃም እንዲሁም በሽተኛ ሊሆን ይችላል። 3ኛ ዩሐንስን

«የብልጽግና ወንጌል» ሰባኪዎች የሚጠቀሙበት በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሰ ምድራዊ ብልጽግና የሚናገር ብዙ ሥፍራ ስለሌለ ነው። በብሉይ ኪዳን ምድራዊ ብልጸግና ሰዎች ያገኙ የነበሩት ታዛዥች በመሆናቸው ሲሆን፣ ከርበቶበ ግን ይህንን አሰበተማረም።

«የብልጽግና ወንጌል» ሰባኪዎች «እግዚአብሔር እንደኛ ደረጃ ኑሮ እንድንኖር ጠርቶናል፣ እራብ እንጂ ጅራት አሰደርግህም ብሎ ተስፋ ሰጥቶናልና ወሽዋሽ ኑሮ መኖር የሰብንም» የሚሉ ናቸው። ስለ ሆነም ቤታቸው፣ መኪናቸው፣ በጠቅለሰው ኑሮአቸው ፍጹም የናረና መበመር የለቀቀ ነው። ይህንን የመሰለ የህብት ጥማታቸውን ሰማሟለት የማይጠቀሙበት ዘዴ የለም።

